# ለጠፉት
# ውጤታማ ፀሎት



አናሲሞስ አገልግሎት

ሊ ኢ ቶማስ

ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከኪንግ ጀምስ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
2003 እትም
ሊ. ኢ. ቶማስ
ሁሉም መብቱ የተጠበቀ ነው

ጆን ባፒቲስት ፕሪንቲንግ ሚኒስትሪ አሳታሚ
ሚሊፎርድ ኦሂዮ
ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ

ተርጓሚና አሳታሚ ፡- አናሲሞስ አገልግሎት

@2014 ዓ.ም አናሲሞስ አገልግሎት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
ከአሳታሚው ፍቃድ ባልተገኘበት ሁኔታ የዚህን መጽሐፍ የቱንም ክፍል መውሰድም ሆነ በየትኛውም መንገድ ማብዛትም ማሰራጨትም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

Onesimus Ministry
አናሲሞስ አገልግሎት
መስከረም 2014 ዓ፣ም
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር ፡- 1113491168

የአታሚው ስምና ድርጅት፡-
ግሎሪ የህትመት አገልግሎት

# ማውጫ

ማውጫ i

ምዕራፍ 1

አስፈላጊነትን መረዳት ....................1

ምዕራፍ 2

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ....................4

ምዕራፍ 3

የግል ጉዳዮች ....................8

ምዕራፍ 4

ዝርዝር የጸሎት ጥያቄዎች....................20

ምዕራፍ 5

መንፈሳዊ ውጊያ....................27

ምዕራፍ 6

የግል ሕይወት ምስክርነት....................42

ምዕራፍ 7

ቃል ኪዳን ማድረግ ....................51

የጸሎት ርዕስ ቅጽ....................54

ዋቢ መጻሕፍት ....................56

# መቅድም

ጸሎት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የምናደርግበትም የምንሰራበትም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሳሪያ እና ትዕዛዝ ነው፡፡ የጠፋው የሰው ዘር ድነት ያገኝ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ በመበገቴት ስራው ጸሎትን በዋናነት ከመጠቀሙ ባሻገር ወሳኝነቱን ለተከታዮቹ አበክሯል፡፡ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ከጌታ ዘንድ የተሰጣትን ታላቅ የድነት ተልዕኮ  እንደሚገባው የተወጣችው ለቃሉ እና ጸሎት አገልግሎት ባላት አይነኬ አቋም ነው፡፡

“ለጠፉት ዉጤታማ ጸሎት “በመጽሐፍ ቅዱስ መርህ ላይ በመመስረት ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠው ድነት በጸጋው ያገኙ ዘንድ ጸሎት አስፈላጊም ወሳኝም መኾኑን ያስገነዝባል፡፡ የግል ህይወት ምስክርነትን ዋቢ በማድረግም አንባቢያን ለጠፉ ሰዎች መዳን ብርቱ የጸሎት ሰራዊት እንዲኾኑ ፣ በዚህም ቃል ኪዳናቸውን በመጠበቅ ንቁ ጸላይ የወንጌል ሠራተኞች እንዲሆኑ ያበክራል፡፡

ለጠፉት ነፍሳት ያለን ፍቅር እንድንጸልይላቸው ከሚያደርጉ ውድ ምክንያቶች የመጀመሪያው ነው፡፡  ጸሎት በአለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ ይልቅ ተጽዕኖ አድራጊ ኃይል ያለው ትዕዛዛዊ ሥራ ነው ፤ አማኞች ሲጸልዩ መልካሙን ለመሥራት ብሎም ወደ ውጤታማነት ለመድረስ ችሎታቸውን ሺህና መቶ ሺህ እጥፍ ይጨምራል፤ ይህ ማጋነን አይደለም! ሰው ሲጸልይ እግዚአብሔር ይሰራል፡፡

የአናሲሞስ አገልግሎት “በክፉ እስራት ያሉ ተጋላጭ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችና ሌሎችን በወንጌል ሁለንተናቸውን በመድረስ የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ ሆነው የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ እየሰራ ይገኛል ፡፡ በደቀመዝሙርነት፣ በአውዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት ዘዴ፣ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ፣ የወጣቶች ሁለንተናዊ ዕድገት ፣ ቤተክርስቲያን ተከላ እና ሚሲዮናዊነት ዙሪያም ውጤታማ ስልጠናዎችን ለተለያዩ ቤተ-ዕምነቶችና መሰል ድርጅቶች ሰጥቷል፡፡ ይህ ግሩም የትርጉም መጽሐፍ የቤተክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮች እና ምዕመናን ለጠፉ ነፍሳት መዳን ታላቅ ወንጌል ስራ

ጸሎት ያለውን ዐብይ ድርሻ በማስገንዘብ ለእግዚአብሔር መንግስት ስራ እንዲነቁ፣ እንዲነቃቁም በማለም ተሰናድቷል፡፡

መጽሐፉ በዚህ መልክ እንዲዘጋጅ የጽሑፍ ስራውን ወ/ሮ እመቤት ዳርጌ፣ ትርጉም አቶ አንድነት መዓዛ እንዲሁም አጠቃላይ የአርትኦት አበርክቶ አቶ ተካ አምባቸው (ወ/ዊ) ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ የትርጉም ስራው እንዲታተም በመፍቀድም የገንዘብ ድጋፍ በማድረግም ለተጉ ኢንቫጀሊዝም ሪሶርስ፤ የመጨረሻ ጽሑፍ ንባብ ስራ ለሰሩ እናት የትርጉም ስራ ብሎም ለግሎሪ ማተሚያ ባለቤት አቶ ክሩቤል፣ ለመላው አናሲሞስ ሰራተኞች፣ የቦርድ አባላት ፣ አጋር ቤተዕምነቶች እና ድርጅቶች ሁሉ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ለጠፉት ነፍሳት የውጤታማ ጸሎት ዋና ምሳሌያችን ነውና.... አንባቢያን ይህን ግሩም መጽሐፍ ገንዘባቸው በማድረግ ለብዙዎች መዳን ተዋጊ የጸሎት ስራዊቶች እንዲኾኑ፣ በዚህም ለጠፉ ነፍሳት በሚደረግ የክብር እና የኃይል ውጤታማ ጸሎት እንዲቀላቀሉ በእጅጉ እናበረታታለን፡፡

**ዶ/ር ነጋ መዓዛ**

**የአናሲሞስ አገልግሎት መስራች**

# ምዕራፍ 1
# አስፈላጊነትን መረዳት

አንድ ሰው የማይጸልይላቸው ከሆነ የጠፉት በርግጥ አይድኑም፣ ሊድኑም አይችሉም። ይህ አባባል አስደንጋጭ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ የጠፉቱ የዲያብሎስ ልጆች (ዮሐንስ 8፡44) ፣ በሰይጣን ግዞት ሥልጣን ሥር እስረኞች (የሐዋሪያት ሥራ 26፡18)፣ በኃይለኛው ቤት ታጋቾች (ማርቆስ 3፡27)፣ የጦርነት ምርኮኞች (ኢሳያስ 14፡17) እንዲሁም ወንጌልን በራሳቸው የማይረዱ (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡3-4) የመሆናቸውን ትልቅ ስእል እስካልተገነዘብን ድረስ የማይታመን ሐሳብ ሊመስል ይችላል።

የጠፉት የደህንነት ተስፋ እንዲያገኙ ከተፈለገ መጸለይ አለብን። ለጊዜው በመንፈሳዊ እውርነት ላይ እናትኩር። 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡3-4 "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብር ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ አለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" ይላል። ክፍሉ በግልጽ የሚያስተምረን ሰይጣን የጠፉ ሰዎችን አእምሮ ወንጌልን እንዳይረዱት በማድረግ እንዳጨለመ ነው።

ሌዊስ ስፔሪ ቻፌር እንዲህ ብሏል "በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡3-4 የተጠቀሰው የአዕምሮ መጨለም ወይም ዕውርነት በአለም አቀፍ ደረጃ የደህንነትን መንገድ ማቀፍ እንዳይችል ያደረጋል፤ የእግዚአብሔርን የማዳን ስራ ትልም በማደናቀፍም ሰው የእግዚአብሔር ዋና ጠላት እንዲሆን ይዳርጋል። የሰው ልጅ ኃይል ሊኖረው የማይችለው የአምዕምሮውን ሐሳብ አቅጣጫ መቃረን ነው'' (ቻፌር፣ 57) ።

በአለማችን ላይ ከተነሱ ታላላቅ ሰባኪዎች አንዱ ቻርለስ ኤች ስፐርጅን ነበር። ስለመለወጡ ሲናገር "እኔ በቅድስና መንገድ መመራትን፤ በመኝታ ጊዜዩም በጸሎት በተሞሉ እጆች ስር ማረፍን፤ ስለ ኢየሱስ በሚናገሩ መዝሙሮች በመታገዝ እንደምተኛ መግለጥ እወዳለሁ። ወንጌልን በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ በኃይል በመጣ ጊዜ፣ ልክ በመካከለኛው አፍሪካ እንዳልተጎበኙ ብሔሮች ውስጥ እንዳለሁ፣ ከፈጣሪ የደም ሥሮች እንደ ጅረት በመውረድ በደም የተሞላውንና የሚያድነውን የማንጻት

ወሬ ፈጽሞ እንዳልሰማ እንደ አዲስ ሰው እሆናለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ እኔ ወንጌል በሰማሁና ነፍሴ በዳነች ጊዜም ከዚህ በፊት ምንም እንዳልሰማሁ አይነት ሰው ነበር ያሰብኩት። ይኸውም ሰባኪው በእውነት እንዳልሰበከ ነበር የቆጠርኩት፤ ይሁን እንጂ ወደ ኃላ ስመለከት ወንጌል ከመቶ ጊዜ በላይ ሲሰበክ፣ በሙላት እንደሰማሁ እንዳምን አድርጎኛል፤ ልዩነቱ ይሄ ነበርና! ከዚህ ቀደም እንዳልሰማሁ አድርጌ እሰማ ስለነበር መልዕክቱ በራሱ እንደ ቀድሞ ጊዜያት ግልጽ አልሆነም:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ኃይል ጆሮቼን በመክፈት መልእክቱን ወደ ልቤ እንዲገባ አደረገ፤ በዚህም እውነቱ ከዚህ ቀደም ተሰብኮ እንደማያውቅ አሰብኩኝ፡፡ አሁን ግን ብርሃኑ በአይኔ ላይ ሁል ጊዜ እንዳበራ ይሰማኛል፤ ዕውር ግን ነበርኩኝ:: ስለዚህ ብርሃኑ እዚያ በጭራሽ እንዳልደረሰ አድርጌ ነበር የማስበው:: ብርሃኑ ሁልጊዜ ይበራ ነበር፤ ሆኖም ብርሃኑን የምቀበልበት አቅም አልነበረኝም፤ ለመለኮታዊ ብርሃን ጨረሮች የነፍስ አይን ዝግጁ አልነበረችምና" (ስፐርጅን 26-28) ።

የስፐርጆን ምስክርነት ለወንጌል እውር ለሆነ አዕምሮ ወንጌል በራሱ ብቻ ምንም አይነት ውጤታማ እንዳልሆነ ማሳያ ነው:: ማንም ጸልዮላቸው ለማያውቃቸው ሰዎች ወንጌል ማካፈል፣ አይነ ስውር ከአንተ ጋር ሆኖ ሳለ የምትጠልቀዋን ፀሐይ እንዳያይ ማድረግ ነው:: ይህ ተስፋ የሌለው ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ታውሮአልና ማየት አይችልም::

መንፈስ ቅዱስ ሰይጣን ያሳወረውን መጋረጃ ካላስወገደ፣ ለወንጌልም አዕምሮንና ልብን ካልከፈተ መዳን አይቻልም፤ የእግዚአብሔር ነገር "ለእርሱ ሞኝነት" ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡14) ። ሞኝነት በግሪኩ "ሞሪያ" ሲሆን፣ "ሞሮን" (ደደብ ወይም የአዕምሮ ችግር ያለው) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይወክላል:: በእንግሊዝኛው የዌብስተር መዝገበ ቃላት ከፍተኛ የአዕምሮ ዘገምተኝነት ወይም ብቃት ማነስ ጋር በማገናኘት ይፈታዋል:: የጠፋ ሰው ወንጌልን የሚያየው እንደ ደደብ ወይም አዕምሮ ችግር እንዳለው ሰው በመሆኑ፣ ለወንጌል ያለውን አሉታዊ ዝንባሌ በሕይወቱ መለወጥ የሚችለው "ጠንካራው የጸሎት ሰው" ነው::

በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ማንም ለማይጸለይለት የጠፋ ሰው ወንጌልን ማካፈል ጎጂ እንጂ አንዳች ጥቅም የለውም:: ጄሲ ፔን ሌዊስ "ከሐሳብ በስተጀርባ ኃይለኛ ክንድ ያለውን ጠንካራ ሰው (ለወንጌል ጨለምተኝነትን

የሚፈጥረውን) ካልተረዳን፣ ሰዎችን ከጨለማ በማውጣት ወደ እግዚአብሔር ውድ ልጅ መንግሥት ሰዎችን ማምጣት ያዳግታል።

እኛም የጌታን ማስጠንቀቂያ ይኸውም በመጀመሪያ ኃይለኛውን ሰው የማሰር ጉዳይ እስካልተረዳን ድረስ ንብረቱን ለመበዝበዝ መሞከር ይበልጥኑ ብስጩነቱን በመጨመር ትጥቁንም ይባስ ማጠናከር፣ ዙፋኑንም በሰላም እንዲጠብቅ ማድረግ ይሆናል" (ፔን ሌዊስ 42-3) ። ለሚድኑ ነፍሳት የመጸለይን አስፈላጊነት ከተረዳን እንዴት መተግበር እንዳለብን መማር ግድ ይላል። እ.ኤ.አ. በ1979 ፉልነስ መጽሔት ላይ ማኔሊ ቤኣሲሌይ "ለጠፉ ነፍሳት መጸለይ" በሚል ርዕስ ጽፏል። ንግግሩንም እንዲህ በሚል ይጀምራል፡ "ለጠፉት መጸለይ የሚለው በብዛት ተደጋግሞ የተነገረ ሐሳብ ነው፤ ይሁን እንጂ እውቀቱና መረዳቱ ጥቂት ነው" ። ይህ በሚስጥራዊ ቁጥር የተዘጋ ካዝና ቁጥሩን ሳያውቁ ለመክፈት እንደመሞከር ይቆጠራል፤ ምንም ያህል ሙከራ ብናደርግ ተስፋ እንቆርጣለን እናቆማለንም።

ለዘላለም መንግሥት ለማዘጋጀት ክርስቶስ የሞተላቸው ነፍሳት ቁም ነገሮቻችን ሊሆኑ ይገባል፤ ለእነርሱ ውጤታማ ጸሎት እንዴት ማድረግ እንዳለብን መማር ይኖርብናል። እንደ እውነቱ ከሆነ የአንተ ጸሎት ነው አንዳንዶችን ከሲዖል መንገድ የሚመልሰው! ታዋቂው የመንፈሳዊ መነቃቃት ሰው ቻርሌስ ጂ ፊኔ "ትዕግሥት ያጣ ኀጢኣተኛን በተመለከተ ከሲዖል መትረፍ የሚችልበት መንገድ ቢኖር፣ ለዚያ ግለሰብ አንተ የምታደርገው ጸሎት ነው" (ፊኔይ፣ 54) ።

ኢየሱስ አባቱ ሲያደርግ ያየውን ነበር እርሱም የሚያደርገው (ዮሐንስ 5፡19) ፣ እኛም እንደዚሁ ጌታችን የሚያደርገውን ብቻ ማድረግ ይኖርብናል። እርሱ ምን ያደርግ ነበር? እርሱ ሁልጊዜ ይማልዳል (ዕብራውያን 7፡25) ፤ ብዙውን ጊዜ አማላጅነት የአንዳንድ ክርስቲያኖች ድርሻ ብቻ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ትልቅ ስህተት እንሰራለን፤ ይህ ኃላፊነታችንን አለመወጣት ማሳያ ነው። እኛ ሁላችንም ጌታችን ለሌሎች የሚጸልየውን አብይ ምሳሌ መከተል ይኖርብናል። ለጠፉት ውጤታማ ጸሎትን እንማር፤ ትልቁን ሥራ አብረን ለመሥራት ከጌታ ጋር እንሳተፍ!

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት

የውጤታማ ጸሎት አንዱና ትልቁ መንገድ ጸሎታችን እንዲመለስ በእግዚአብሔር ፊት ጠንካራ የሆነ ምክንያት ማቅረብን ነው:: ይህን እንድናደርግ በኢሳይያስ 41፡21 ላይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡- "ክርክራችሁን አቅርቡ ይላል እግዚአብሔር፤ ማስረጃችሁን አምጡ፤ ይላል የያዕቆብ ንጉስ::" ጠንካራ የክርክር ምክንያቶች ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረጉ ናቸው፤ ለጠፋት ጸሎት ማድረግን አስመልክቶ አያሌ ጠንካራ የክርክር ነጥቦች አሉ:: ኤፍ ጄ ሁጌል የገለጸበት መንገድ ወድጀዋለሁ፡- "ወንጌልን በማወጅና በክርስቶስ መንግሥት ቀጣይነትና ዙሪያ የእግዚአብሔርን አላማ ለመደገፍ የልመና መንገድ ብናገኝ፣ በመንፈስ መጸለይ እንጀምራለን፤ የጳውሎስን 139፣ ዴቭድ ብራንድን፣ ጆርጅ ሙለር ወይም ፕሬይንግ ሁድ ጸሎትን እናጠናክራለን:: በዚህም ጸሎታችን ይሰማል፤ ታላቅም ነገር ይሆናል" (ሁጌል ፣80) ::

ለጠፉት ያለን ፍቅር ለእነርሱ እንድንጸልይ ከሚያደርጉ ምክንያቶች የመጀመሪያው ነው:: ጸሎት "ፍቅር በጉልበቷ ላይ" እንደሆነች ይገልጻል:: በእርግጠኝነት ኢየሱስን ወደ መስቀል የወሰደው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር ነው:: በሲኦል ያለውን ባለጠጋ ሰው፣ ወንድሞቹ ወደዚህ የስቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ለወንድሞቹ እንዲማልድ ያደረገው ለአምስቱ ወንድሞቹ ያለው ፍቅር ነው (ሉቃስ 16፡ 27-28) :: ፍቅር ወደ ምልጃ ስፍራ ወይም ሕይወት ይመራናል::

በችካጎ ያለው ታሪካዊው ፓስፊክ ጋርደን ሚሽንን እግዚአብሔር በሲኦል ገደል ላይ እየተንገዳገዱ ያሉትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለማዳን ተጠቅሞበታል:: ይህ ድርጅት "የእናቶች ጸሎት ተከትሎሃል" የሚለውን ማሳሰቢያ በውስጡ ቢያካተት አይደንቅም:: በእናቶች የእንባና የፍቅር ጸሎት የተለወጡትን አስገራሚ የነፍሳትን ቁጥር የሚገልጸው ዘላለም ብቻ ነው:: በርግጥ ፍቅር ነፍሳትን በማዳን ሥራ ያለን ትልቁ ሐብታችን ነው:: እምነት ደግሞ ለጠፉ ነፍሳት የምንጸልይበት ሌላኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት

ነው። ኢየሱስ “ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል” ብሏል (ማርቆስ 9፡23)። ሁሉ የሚለው ቃል በእርግጠኛነት የሚያካትተው የነፍሳት መዳንን ነው። ለአንድ ሰው መዳን እግዚአብሔርን ማመን ከቻልክ ማግኘት ትችላለህ።

አራቱ ሰዎች ሽባውን ሰው ወደ ኢየሱስ ባመጡ ጊዜ እምነታቸውን አይቶ “ልጄ ኃጢአትህ ተሰርያለች” አለ (ማርቆስ 2፡5)። እርሱ እንዲፈወስ ቢያመጡትም እንኳ የኃጢአቱን ስርየት ተቀብሏል፤ የእምነት አስደናቂ መገለጫው ይኸው ነው። እምነት የመንግሥቱ ገንዘብ ነውና!

እኔ ለጠፉት ነፍሳት እንዲጸለይ ከተወዳጅ ምክንያቶች እንዱ መጽሐፍ ቅዱስ በጸሎት ውስጥ ያለውን ኃይል መግለጡ ነው። እንደ ያዕቆብ 5፡16 አገላለጽ “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች”። ኃይለኛ ጸሎት በዚህ አለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ ይልቅ ተጽዕኖ አድራጊ ኃይል ያለው መሆኑን መረዳት በራሱ ከባድ ነው።

“ጸሎት ከሰዎች መረዳት ያለፈ፣ የላቀና የተመረጠ ትእዛዛዊ ሥራ ነው። ክርስቲያን ሲጸልይ መልካምን ለመሥራት፣ ወደ ውጤታማነት ለመድረስ ያለው ችሎታ ሺህና መቶ ሺ እጥፍ ይጨምራል፤ ይህ ማጋነን አይደለም! ሰው ሲጸልይ እግዚአብሔር ይሰራል” (ሔውጅል፣ 10)።

የአቶሚክ ቦምብ በጃፓን ሁለተኛ የአለም ጦርነት ወቅት በተጣለ ጊዜ በቁጥር 92 ሺህ የሚያህሉ ሰዎች ተገድለዋል። አሶር ኢየሩሳሌምን በወረረ ወቅት ንጉስ ሕዝቅያስ በሕዝቡ ፊንታ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔር መላእኩን በመላክ በአንድ ምሽት 185 ሺህ የአሶር ወታደሮችን ገደለ። የሕዝቅያስ ጸሎት ከአቶሚክ ቦምብ ሁለት እጥፍ አደገኛ ነበር፤ ጸሎት ጠላትን ለመደምሰስ የሚችል ከሆነ፣ ነፍሳትን የማዳን ኃይሉ የላቀ መሆኑ እርግጥ ነው።

እግዚአብሔር ለጠፉት እንድንጸልይ ከሚጠበቅብን ውጭ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት እንኳ ባይኖር ይህ በራሱ በቂ ነው። እግዚአብሔር ለእሥራኤል የሚማልድ አንድም እንደሌለ ባየ ጊዜ በጣም ተደነቀ (ኢሳያስ 59፡16)። እግዚአብሔር የሚጠብቀው አንድ ሰው እንዳለ ክፍሉ ያበክራል።

ስለምልጃ እግዚአብሔርን መፈለግ አንድሪው ሙሬይ የተናገረውን እንመልከት፦ እግዚአብሔር ለሌሎች መጸለይን በሕይወታችን የመጀመሪያው ቀዳሚ ጉዳይ አድርጓል። የእግዚአብሔር የልቡ ጩኸት በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-4 በግልጽ ሰፍሯል፡ “እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፤ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና መኳንንትም ሁሉ እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑ እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይሄ ነው።” መጀመሪያ የሚለው ቃል በግሪኩ ፕሮቶን ነው፤ በስትሮንግ መዝገበ ቃላት የጊዜ፣ በታ፣ ቅድመ ተከተል ወይም የአስፈላጊነት መጀመሪያ እንደሆነ ተተርጉሟል። እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድን ይፈልጋል፤ ማንም ሰው ያለጸሎት መዳን ስለማይችል እኛ ማድረግ ያለብንን ጸሎት ቀዳሚ ስፍራ ላይ ማስቀመጡ ያስገርማል?

ለጠፉ ነፍሳት እንድንጸልይ ማበረታቻ ከሚሆኑን ነገሮች አንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ናቸው። ከሁሉም ምሳሌዎች የላቀው ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ በኢሳይያስ 53 ላይ ያለው ትንቢት ክርስቶስ “ለበደለኞች ማለደ” ይላል። ይህ ትንቢት በቀጥታ ተፈጻሚነት ያገኘው እርሱ በመስቀል ላይ “አባት ሆይ እነርሱ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” ባለ ጊዜ ነው (ሉቃስ 23፡34) ።

ኢየሱስ እኛ ለሌሎች መጸለይ እንዳለብን አይነተኛው ፍለጋችን ነው፤ አሁንም እያደረገው አለ። አዳኛችንና ጌታችን በሰማይ ዙፋን የተቀመጠ፣ የነገሥታት ንጉስ ሆኖ ሳለ አሁንም ለሌሎች መጸለዩን ቀጥሏል። በዕብራውያን 7፡25 ያለው ሐሳብ ይመስጠኛል፦ “ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፣ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይቻላል።”

ሐዋሪያው ጳውሎስ ልንከተለው የሚገባ ሌላኛው ምሳሌያችን ነው። በሮሜ 10፡1 ላይ ርህራሄውን ሲገልጽ “ወንድሞች ሆይ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እሥራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።” አር አርተር

ማቲው “Born for Battle” (ለጦርነት መወለድ) በተባለው መጽሐፋቸው ጸሎትን እንዲህ ያብራራሉ፡-

“እግዚአብሔር ሰዎች በክፍተቱ ቦታ በመቆም በራሳቸው ኃጢአትና ተፈጥሮአዊ ሕይወት የእግዚአብሔርን የበላይነት የማይቀበሉትን ለመፈለግ የሚደረግ የመጨረሻ መለኮታዊ ፍለጋ ነው” (ማቴው፣ 104) ። ብቸኛው ጥያቄ “እኛስ እነርሱን እንከታተላለን ወይ?” የሚለው ነው።

ለእንደነዚህ አይነት የምልጃ ጸሎት የሚሆኑ ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያላቸውን ክፍሎች መጥቀስ ቢቻልም፣ አንድ ብቻ ለማከል እወዳለሁ። ይኸውም እግዚአብሔር ኃላፊነቱን የእኛ አድርጎታል የሚል ነው! የእግዚአብሔር “ቅዱስ ካህናት” አካል ያደረገን (1ኛ ጴጥሮስ 2፡5) ለሌሎች ኃላፊነት እንዲኖረን ነው፤ ምክንያቱም ካህናት ምድርን ወክለው ሰማይ የሚቀርቡ ናቸውና። የእኛ ተቀዳሚ ተግባር የሚሆነው በእግዚአብሔርና ሰው መካከል በመሆን የሰዎችን ጉዳይ በምልጃ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው። አሮንም ያደረገው ይሄንኑን ስለነበር በእሥራኤል ኃጢአት ምክንያት የመጣውን መቅሰፍት በሕያዋንና በሙታን መካከል ይዞ በመቆም መቅሰፍቱን አቆመ (ዘኁልቁ 16) ።

የዳንን እኛ ሁላችን ካህናት እንደመሆናችን መጠን ሁላችንም ለጠፉት የመማለድ ኃላፊነት አለብን። ይህ ካልሆነ ግን እነርሱ ለዘላለም በእሳት ባህር ውስጥ ይቆያሉ። ስለዚህ እንዲህ የሚለው የኤስ ዲ ጎርዶን ጥብቅ የሆነ ምልጃ በልባችን እናኑር፡- “በውስጤ ያለውን እምነት መቋቋም አልችልም፤ ይህን ስል ደስተኛ አይደለሁምና! ያንተን ወይም የእኔን ስሜት ባልሰማ ይሻላል፤ ይሁን እንጂ አንድ ሰው በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ካለመቻሉ የተነሳ፣ በዚህች በወደቀች አለም ውስጥ ጠፍተው ያሉ ሰዎች እንዳሉ እውነታውን መቋቋም አልችልም” (ጎርዶን፣ 194-195) ። የእኔ ጸሎት እነዚህ ኃይለኛ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች አነሳስተውህ፣ ከዚህ በፊት እንደምትጸልየው ሳይሆን፣ በተለየ መልኩ መጸለይ እንድትችል ነው።

# ምዕራፍ 3
# የግል ጉዳዮች

በማንኛውም የተመለሰ ጸሎት የሚካተቱ ሁለት ሁኔታዎች አሉ፡- ጽድቅና እምነት! በፈሰሰው ደሙ በኩል የመጣው የክርስቶስ ጽድቅ በጸጋው ዙፋን ፊት በድፍረት እንድንቀርብ ያደርጋል፤ ይህ ለውጤታማ ጸሎት እጅጉን አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ ግላዊ ጽድቅም ወሳኝ ጉዳይ ነው። መዝሙር 66፡18 "በልቤስ በደልም አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር" ይላል። ምናልባት ይሄን ሐሳብ በዮሐንስ 15፡7 "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል" በማለት ኢየሱስ በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል። በሌላ አገላለጽ ታዛዥ የሆኑ ክርስቲያኖች የጸሎታቸውን መልስ ያገኛሉ።

በተመለሰ ጸሎት ሌላኛው አስፈላጊ ነገር እምነት ነው። በመንፈሳዊው አለም መቼም መዘንጋት የሌለበት ሕግ ነው። ሁል ጊዜ "እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ" (ማቴዎስ 9፡29) እንደሚለው፣ አለማመን ሁል ጊዜ የማያቋርጥ ኃጢአታችን በመሆን፣ ላልተመለሰ ጸሎት ምክንያት ከመሆን ያልፋል።

ስለዚህ ለጠፉት በምንጸልይበት ጊዜ ጽድቅና (ምክንያታዊና ግላዊ) እና እምነት ያስፈልገናል። በተጨማሪ ለዚህ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ስምንት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው የተሰበረ ልብ ነው። "በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ" የሚል የመንፈሳዊ አጨዳ ህግ ነው። ሆኖም ብዙ ጊዜ የምንፈልገው ምርቱን ያለ ልብ ስብራት ማጨድን ነው። አንድ ጊዜ ሊኖርድ ሪቬንሂል ሲናገር "እግዚአብሔር ብዙ ጸሎቶችን አይመልስም፤ ምክንያቱም ጸሎቶች በግል ፍላጎት ላይ የተጣበቁ ወይም የግል ጥቅም ላይ ያተኮሩ ስለሆነ ነው። እርሱ አስፈልጊ የሆኑ ጸሎቶችን ይመልሳል" (ሪቬንሂል፣ 110)። ለነፍሳችን አስፈላጊውን እንስከምናገኝ ድረስ ሌሎች ጸሎቶቻችን ላይመለሱ ይችላሉ። ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም እንዳለቀሰ ሁሉ እኛም እጅግ ለምንወዳቸው ለጠፉ ወገኖቻችን ማልቀስ ይኖርብናል።

በአንድ ወቅት አንዳንድ የደህንነት ሰራተኞች ለበላይ አለቃ ነፍሳትን በማዳን ውጤታማ እንዳልሆኑ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም በመጠየቅ ጽፈው ነበር። እርሱም "በእንባ ሞክሩ" ብሎ ሁለት ቃላትን የያዘ መልዕክት ላከ። እንባ

ወንጌል በማብሰር የሚጣመር በጣም ጠንካራ የሆነ ነገር ነው፤ እግዚአብሔር ውጤታማ ምርትን ይሰጣል (መዝሙር 126፡5-6)።
ሌላኛው አስፈላጊ ነገር ምጥ ወይም ጭንቅ ነው። በኢሳያስ 66፡8 የስቃይና ጭንቅ ስእላዊ ገለጻ ተጠቅሷል፡- "…ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆቹዋን ወልዳለችና" ። የስትሮንግ መዝገበ ቃላት "በምጥ፣ በጭንቅ ወይም በጥልቅ ኃዘን ስቃይ መውደቅ" የሚለውን ፍቺ ያስቀምጣል። ሉቃስ 22 ኢየሱስ በታላቅ ጭንቅ ውስጥ እንደነበር፣ የደም ላብ እንዳላበው ይናገራል። ብዙዎቻችን በጸሎት ሕይወት ወደዚህ ደረጃ አልደረስንም፤ ለዚህም ነው ነፍሳትን ለክርስቶስ በመማረክ ጥሩ ውጤት ማግኘት ያልቻልነው።
የኢየሱስ ድነት "ዳግመኛ ልደት" እንደሆነ አስተምሯል። እናት በሥጋ ልጁዋን በምትወልድበት ጊዜ ምጥ ብርቱ ጭንቀት እንደሚሰማት ሁሉ፣ በመንፈሳዊው አለምም እንደዚሁ ነው። ጳውሎስ ለገላቲያ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ካለመብሰል የተነሳ ለክርስቶስ መማርክ ሲል በወሊድ ጭንቅ ምጥ ውስጥ እንዳለ ይገልጻል። ምንም እንኳ ባል ልጅ ስለማይወልድ ሚስቱ በምጥ ጊዜ የምታየውን ስቃይ እንደማይረዳው ሁሉ፤ ዘጠና አምስት ከመቶ የሚያህሉ አማኞች ለክርስቶስ ምንም ነፍስ ስለማይማርኩ፣ ለነፍሳት ያለውን የምጥ ጭንቅ አይረዱትም።
ለእኔ ጀግና ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ በህንድ አገር ሚሲዮናዊ በመሆን ነፍሳት እንዲድኑ ሕይወቱን ለጸሎት አሳልፎ የሰጠው ጆን ፕሬይንግ ሐይድ ነው። በ1908 በየዕለቱ እግዚአብሔር የሚድኑ ነፍሳት እንዲሰጠው ይጸልይ ነበር። በዚህም በተጠቀሰው አመት አራት መቶ ሰዎችን ለጌታ ኢየሱስ ማረከ፤ በሚቀጥለው አመት በየቀኑ ሁለት ነፍሳት እንዲድኑ ጸልየ (ጸሎቱ ለመጸለይ ያህል ብቻ ሳይሆን፣ እንዲጠመቁና ለክርስቶስ የተለዩ እንዲሆኑ ጭምር ነበር)፤ ከስምንት በላይ ሰዎችን ለክርስቶስ ማረከ። በ1910 ዓ.ም እ.ኤ.አ በየቀኑ አራት ሰዎች እንዲድኑ ጸልዮ እግዚአብሔር ጸሎቱን አሳካለት። ይሁን እንጂ በዚህ አመት የጤናው ሁኔታ ችግር ሲገጥመው ኀደኛው ዶክተር ጋር እንዲሄድ በብዙ ገፋፍቶት ነበር። እኛ መረዳት እንድንችል ለነፍሳት በእጅጉ ለሚጨነቀው ሰው ዶክተሩ ምን እንዳለው እስቲ እንስማ፡- "ልብህ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው፤ እኔ እንዲህ ያለ አስቸጋሪ ሁኔታ አጋጥሞኝ አያውቅም። ልብህ በትክክለኛ ቦታ በስተግራ በኩል ሳይሆን ያለው

የተፈጥሮ ቦታውን ለቆ በስተቀኝ ሥፍራ ይገኛል። ይህ እንዲህ ሊሆን የቻለው ከብዙ ሐሳብና ጭንቀት ስለሆነ፣ ወደ ትክክለኛ ቦታውና ሁኔታ ለመመለስ ለወራት ያህል ጸጥ፣ ዝግ ያለና የተረጋጋ ሕይወት መኖር ያስፈልጋል። ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ካልለወጥክና ድካምህን በቃ ካላልከው በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከፍተኛውን ቅጣት ትከፍላለህ" (ኬር፣ 44) ። ነፍሳትን ከጨለማ በማዳን ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ከተባበርን መክፈል ያለብን ዋጋ አለ። ስለዚህ "ሕይወታቸውን እስከሞት ድረስ የማይወዱ" ውድ የሆኑ ቡድኖችን እንቀላቀል (ራዕይ 12፡11) ፤ ይህን ካደረግን ድል የእኛ ይሆናል!

የጠፉ ነፍሳትን መከራ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በስዕላዊ መልክ በጸሎት መትጋትና መጽናናት ወሳኝ ነገር መሆኑን ያስረግጣል። ኢሳያስ 14፡17 የጠፉ ሰዎች የሰይጣን እስረኞች በመሆናቸው ሊለቃቸው እንደማይፈልግ ይነግረናል። ሐዋሪያት ሥራ 26፡18 በሰይጣን አገዛዝ ወይም ሥልጣን ሥር መሆናቸውን ይገልጻል፤ ከሁሉ የሚበልጠው አስፈሪ ገለጻ ጌታ ኢየሱስ በማርቆስ 3፡27 የኃይለኛው ቤት በማለት ሲገልጸው እንመለከታለን። ይህ የሚያመላክተው ኃይለኛው ካልታሰረ በቀር ማንም እንድን ሰው እንኳ መርዳት እንደማይቻለው ነው።

በአንዳንድ ኃይለኛ አጋንንቶች ላይ ድልን ለማግኘት ጾምና ጸሎት አስፈላጊ ነው (ማርቆስ 9፡29) ። ቀጣይነት ያለው ጠንካራ ጸሎት የሚያስፈልገው እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ለማዳን ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም፤ ሰይጣን ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆነ እንጂ! ሰይጣን አንድን አገርና ባህል ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠር ይችላል። ለዚህም ነው አንዳንድ ሚሲዮናዊያን በአንዳንድ አካባቢ ያሉ ሰዎችን በወንጌል መድረስ የሚከብዳቸው። "ኬሪ በሕንድ የመጀመሪያውን አማኝ በውሃ ከማጥመቁ በፊት ብዙ አመታት ተቆጥሯል፤ ጀድሰን በቡርማህ የመጀመሪያውን ደቀመዝሙር ለክርስቶስ ከመማረኩ በፊት ሰባት አመታት ወስዶበታል፤ ሞሪሶን የመጀመሪያውን የቻይና አማኝ ወደ ክርስቶስ ከማምጣቱ ሰባት አመት ቀደም ብሎ መከራ ተቀብሏል። ሞፋት በአፍሪካ ያሉትን ቡችማኖች በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ከመድረሱ ቀደም ብሎ ሰባት አመታትን ጠብቋል። ሄኔሪ ሪቻርድስ የመጀመሪያውን አማኝ በበንዛ ማንታካ ኮንጎ ከመምጣቱ በፊት ሰባት አመት ሙሉ መከራና እንግልት አሳልፏል። (ጎርዶን፣ 139-40)።

የሰይጣን አንደኛውና ተወዳጁ ዘዴ ሁኔታዎች የማይቻሉ እንዲመስሉ በማድረግ ተስፋ በመቁረጥ ጸሎት እንድናቆም ማድረግ ነው። ይህን የሚያደርገው ጸሎትን በፍጹም መከልከል ስለማይችል ነው። በድሮ ጊዜ “ሰይጣን አንድ ደካማ ክርስቲያን በጉልበቱ ሲንበረከክ ሲያይ ይንቀጠቀጣል” የሚለው አባባል ትክክል ነው። ሁሉም ጸሎት ውጊያ ነው፤ አንተ በምትጸልይበት ጊዜ ምንም እንኳ በሁኔታዎች ለውጥ ባታይ ሰይጣን እየተሸነፈ መሆኑን መገዘብ ይኖርብሃል።

በምንጸልይበት ጊዜ በመንፈሳዊው አለም ምን እንደሚሆን ብናስተውል በብዙ እንበረታታ ነበር። ኤልሳዕ ከጠላት ይጠብቃቸው የነበረውን ሰረገላና ሰራዊት ማየት እንዲችል የአገልጋዩን አይኖች እንዲከፍት እንደጸለየ፣ አይኖቻችን በቅጡ ሊከፈቱ ይገባል (2ኛ ነገስት 6፡17) ። ለጠፉ ሰዎች ውጤት ብታይ ባታይ ጸሎትህን ቀጥል፣ የጸሎትህ መልስ እየተመለሰ ነውና።

እንደዚህ አስደናቂ የሆነ ቀጣይነት ያለው ትጋት የሚታየው በጆርጅ ሙለር ሕይወት ነው። እርሱ በአገልግሎቱ ጅማሬ የጸለየላቸው ሰዎች ወዲያውኑ ወደ ደህንነት ሲመለሱ ውጤታማ መሆኑን በማየቱ ነገሮች ሁሌም እንዲህ ይሆናሉ የሚል ትልቅ የመገረም ስሜት ገባው። ይሁን እንጂ የእርሱን ስሜት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ንግግሩ እንመልከት፡- “ጌታ ኢየሱስን ባመንኩባቸው አምሳ አራት አመታት ከዘጠኝ ወራት ሰላሳ ሺ የሚያህሉ የጸሎት መልሶችን አግኝቼ ቢሆን ኖሮ፣ ይህን ያህል ሩቅ መንገድ ዘልቄ መሄድ አልችልም ነበር። አንዳንዶች ምናልባት የእኔ ጸሎት ሁሉ ተመልሷል ብለው ያስቡ ይሆናል፤ እውነቱ ግን ይህ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ሳምንታትን፣ ወራትን ወይም አመታትን መጠበቅ ነበረብኝ። በኖቬምበር 1844 አምስት ሰዎች እንዲለወጡ መጸለይ ጀመርኩኝ። ሌላ ተልዕኮ ሳይኖረኝ በየዕለቱ በጤንነት ይሁን በሕመም፤ በባሕር ላይ ይሁን በየብስ፤ በማንኛውም አይነት ሁኔታ ግፊት ጭምር ውስጥ ሆኜ ጸለይኩኝ። ከእነዚያ አምስቶቹ የመጀመሪያው አንዱ ጌታን ለማግኘት አንድ አመት ከስድስት ወር ጊዜ (ማለትም አስራ ስምንት ወራት) ወሰደ። እግዚአብሔር አመሰገንኩ ለሌሎችም ጸለይኩኝ። ከአምስት አመት በኃላም ሁለተኛው ጌታን ተቀበለ። ለሁለተኛው ጌታን አመስግኜ፣

ለተቀሩት ለሶስቱ መጸለይ ቀጠልኩኝ። ሶስተኛው ወደጌታ እስኪመጣ ድረስ ሌላ ተጨማሪ ስድስት አመታት አለፈ። ለሶስቱ ጌታን በማመስገን ለተቀሩት ሁለት ሰዎች መጸለዩን ቀጠልኩ፤ ነገር ግን እነዚህ ሁለቱ ጌታን ሳይቀበሉ ቀሩ። እግዚአብሔር እንደጸጋው ባለጠግነት በብዙ ሺዎች የሚቆጥሩ የጸሎት መልሶችን ቢሰጥም፣ ለአያሌ ቀናት፣ ሰዓታትና ሰላሳ ስድስት አመታት የተጸለየላቸው ወደጌታ ሳይመጡ የቀሩ ሁለቱ ሰዎች ጉዳይ ግን መልስ አላገኘም" (አስቴር፣ 246-47)።

ሆኖም ይህ የታሪኩ ፍጻሜ አይደለም፤ እርሱ በየቀኑና በየአመቱ መጸለዩን ቀጠለ፤ እንዲህም አለ፦ "ትልቁ ጉዳይ መልሱ እስኪመጣ ድረስ ጸሎትን አለማቋረጥ ነው። ለአንድ ሰው መለወጥ ሰላሳ ሶስት አመታት ያህል ስጸልይ ነበር። አሁን ባይድንም ወደፊት ይድናል! ይህ እውነት ባይሆን እንዴት መጸለይ እችላለሁ"። የሙለር ጓደኛ ጌታን የሚቀበልበት ቀን መጣ፤ ወደ መቃብር አፋፍ በደረሰ ጊዜ ይህ ጓደኛው ልቡን ለጌታ ከፈተ። ትጋትን በተሞላ የማይቋርጥ ጸሎት ውጊያ ድል ተገኘ። የሙለር ውጤታማነት ምናልባት በአራት ኃይለኛ ቃላት ሊጠቀለል ይችላል "እርሱ ተስፋ አልቆረጠም ነበር" (ኤስታማን፣ 99-100)።

ጸሎት ውጊያ ስለሆነ በመማለድ ውስጥ ጠብ እንደመጫር መቁጠር አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር አስገራሚ የሆነ ሥልጣን ሰጥቶናል (ማቴዎስ 16፡19)። የጸሎትን ሥልጣን በተለይ ወንጌልን ለሰዎች በምናደርስበት ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ መታዘዝ አለብን (ማቴዎስ 28፡18-20)። እኛ አሸናፊዎች ነን (ራዕይ 12፡11)፣ "ከአሸናፊዎችም በላይ" (ሮሜ 8፡37)! እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው ኃይለኛና መሉ መሳሪያ ሆነን የጠላትን መሳሪያ እንድናከሽፍ ነው (ሉቃስ 11፡21-22)። ከዚህ በፊት እንዳየነው ሰይጣን ሰዎችን በባርነት ውስጥ የያዛቸው ስለሆነ፣ ያለውጊያ ሊለቃቸው አይፈልግም፤ ሁል ጊዜ ማወቅ ያለብን "የውጊያ መሳሪያዎቻችን ሥጋዊ አይደሉም፤ ነገር በእግዚአብሔር በኩል ኃይለኛ ናቸው" (2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4)፤ በእግዚአብሔር የጦር መሳሪያ ለውጊያ ስንዘጋጅ በጸሎት እንዋጋለን (ኤፌሶን 6፡10-18)።

የሲያልን ደጅ በኃይለኛው እንድትታጠቅና እንድታሸንፍ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን በኃይል አቁሟል። እኛ ግን ያለአንዳች ስራ ቁጭ ብለን ሲያል እንድትሰፋ አፉዋንም ያለገደብ እንድትከፍት አደረግን (ኢሳያስ 5፡14)። “ፈራጅነትና አደገኛነት በተመለከተ በጣም አስቀያሚ የሆነ ልዩነት አለ” በማለት ራቫንሂል የተናገረው ያስገርምኛል።

ትልቁን ዝሆን ትንሹዋ የእንጨት ጉቶ ታቆመዋለች፣ ምክንያቱም እንዳይጠፋ ተደርጎ በዚህ መልኩ ስላሰለጠኑት ነው። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዲሁ ስልጣኗን እንዳትጠቀም በሰይጣን ተታላለች (ኤፌሶን 1፡17-23)። በዚህም የምንወዳቸው ወገኖች በእኛ አለማመንና አለመትጋት ምክንያት እስረኞች ሆነው እንዲቀጥሉ ሆኗል።

ሰይጣን የተሸነፈ መሆኑን በፍጹም መቀበል አይፈልግም። ከእርሱ በላይ እርሱን ለሚገዛው ራሱን አያስገዛም፤ የሚቃረነውን ማንኛውንም ነገር በአጽንኦትና በትጋት ይቃወማል። ስለዚህም በኃይል በመንጠቅ ከእጁ መውሰድ ይኖርብናል (ኒዌል፣ 27) ። ለነፍሳት በኃይል በመዋጋት፤ ለሰማዩ መንግሥት ማብቃት ጊዜው ነው። “መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፤ ግፈኞችም ይናጠቁአታል” (ማቴዎስ 11፡12)።

ወደ መጸለይ በምንመጣበት ጊዜ ምልጃ በብዙ ውጤታማ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ምሳሌዎች አሉ፦ አብርሃም ለሰዶም (ዘፍጥረት 18)፤ ሙሴ ለእስራኤል (ዘፍጥረት 32)፤ ሕዝቅያስ ለይሁዳ (2ኛ ዜና 19)። ምልጃ እግዚአብሔር በጉዳዩ መልስ እንዲሰጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶችን ማቅረብ ነው። እግዚአብሔርም “የክርክር ምክንያቶችን ወደ ፊቱ እንድናመጣ” አዟል (ኢሳያስ 41፡21)።

ኤቲ ፐርሰን እንዲህ ይላል “ጉዳዮቻችንን ወደ እግዚአብሔር ፊት በማቅርብ መከራከር አለብን። ይህ የሚሆነው ግን እሱን በማሳመናችን ሳይሆን፣ እርሱ እኛን በማሳመኑ ነው። ይህን በማድረግ እርሱ በቃሉ፤ መሐላውና ባሕርይው በሰጠን ተስፋ መሰረት በእምነት መጠየቅ እንዳለብን፤ እርሱ ደግሞ ራሱን መካድ ስለማይችል ምልጃችን ይመልሳል በሚሉ ሐሳቦች መሐል ራሱን አስቀምጧል” (ፐሪሴን፣ 150)።

ስፔርጅን ስለ ምልጃ የነበረው ስሜት በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ እርሱ ምንድነው ያለው "በምትጸልይበት ጊዜ ምልጃ ማድረግ የእምነት ልምድ ነው፡፡ "ጸሎት ብቻ የሚሉ ሰዎች የሚጸልዩ አይደሉም፤ ከእግዚአብሔር ጋር መከራከርን ረስተዋልና፡፡ ጉዳዮቻቸውንና የክርክር ምክንያታቸውን በእርሱ ፊት የሚያመጡ ሰዎች በጥያቄዎቻቸው ዙሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ይከራከራሉ፡፡ ውድ ወንድሜ ለተስፋው፤ ለምክሩ መማለድን መማር አለብን፡፡ ሁልጊዜ ስለ አንድ ነገር የምንማልድለት ነገር ሊኖረን ይገባል፡፡ ምልጃ እስካላደረክ ድረስ ጸልያለሁ ብለህ አታስብ፤ ምክንያቱም ምልጃ የጸሎት ዋናው ክፍል ነውና (ስፔርጅን፣ 49-50)፡፡

ጆርጅ ሙለር በመዝሙር 68፡5 ላይ በመጀመሪያ ላይ ያለውን ሐሳብ በመውሰድ "አባት ለሌላቸው አባት" በማለት ቃሉን ወላጅ ለሌላቸው በሚማልድበት ጊዜ ሁሉ ይጠቅሰው ነበር፡፡ እርሱም እንዲህ ይል ነበር "በእግዚአብሔር እርዳታ ይህን ክርክር በፊት አደርጋለሁ፤ እርሱ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ወላጅ የሌላቸው ልጆችን እንዲያከብር፤ እርሱ የእነሱ አባት ስለሆነ፣ ለእነርሱ የሚያስፈልገውን እንዲሰጥ እማጸነዋለው፡፡ የእኔ ድርሻ እርሱ ለእነዚህ ድሃ ልጆች ፍላጎት መገኘት ያለበትን ነገር እንዲያቀርብ ማሳሰብ ብቻ ነው" (ፒሪሰን፣ 143)፡፡

ለጠፉ ነፍሳት መዳን መማለድ እንዳለብን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚናገሩ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ከጊዜና ቦታ አንጻር ጥቂቶችን ብቻ እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ፡፡ የእግዚአብሔር አላማ ለሰዎች ግልጽ እንዲሆን እንማልዳለን (ኤርሚያስ 1፡5፣ ሉቃስ 19፡10፣ 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9፣ የሐዋሪያት ሥራ 26፡18፣ እና ኤፌሶን 2፡5-7)፡፡ ደህንነትን በተመለከተ ያሉ የእግዚአብሔር ተስፋዎች እንዲፈጸሙ እንማልዳለን (ዮሐንስ 3፡16፣ ሮሜ 10፡13፣ ዮሐንስ 6፡37)፤ የእግዚአብሔር ኃይል እንዲያድን መማለድ እንችላለን (ዕብራውያን 7፡25፣ ሮሜ 1፡16፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡4-5 እና 1ኛ ጴጥሮስ 1፡3-5)፤ የእግዚአብሔር ስብዕና ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት እንደ ፈጣሪ፣ አዳኝ፣ አባት እና ጌትነት እንዲገለጥ መማለድ እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርያት፡- ፍቅሩ፣ ምህረቱ፣ ጸጋው፣ ታጋሽነቱና ለሰዎች መቸገሩ ለሰዎች እንዲገለጥ መማለድ እንችላለን፡፡ የእኔ ትልቁ ምልጃ ያለፉ ጊዜያቶችን ለሌሎች የማዳን

ሥራ ማዋል፣ ነነዌ (እግዚአብሔር ለጥፋት የፈረጃት እጅግ ኃጢአተኛ የሆነች ከተማ) እንድትድን፣ በርኩስ መንፈስ ሌጌዎን (ልብስ ሳይለብስ የሚኖር፣ በመቃብር ሥፍራ ማንም ሰው ሊቀርበው የማይችል) ነጻ እንዲወጣ፣ ከማህበረሰብ የተገለለና በርኩስ መንፈስ የሚሰቃይ እኛ ከምናውቀው ከማንኛውም የከፋ ወጥመድ እንዲፈታ፤ የተርሴሱ ሳውል (ቤተክርስቲያን ያሳድድ የነበረ) እንዲለወጥ እንዲሁም ያልተደረሱ ከተሞች በአጠቃላይ በወንጌል እንዲደረሱ ነው (የሐዋሪያት ሥራ 9፡35)።

ሌላው ለአመታት የምናደርገውን ጸሎት ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርገው የእኛ መነሻ ሐሳብ ነው። ለጠፉ ነፍሳት በምንጸልይበት ጊዜ የጸሎታችን ዋና መነሻ ሐሳብ መሆን ያለበት ለእግዚአብሔር ክብር ነው (ዮሐንስ 1፡18)። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ መነሻ ሐሳባችን በትዕቢትና በራስ ወዳድነት የተመረዘ ይሆናል። ወላጆች የጸሎቶቻቸው መነሻ ሐሳብ ጥሩ ስላልሆነ "ጥቁር በጎች" ለሚለው የቤተሰቦቻቸው ስም ሊጸልዩ ይችሉ ይሆናል።

ምንም ውጤት ወይም ለውጥ ሳላይ ለባለቤቴ ወንድም ለአመታት ጸልያለሁ። ይሁን እንጂ እርሱ የካንሰር በሽተኛ እንደሆነ ሲታወቅ ጸሎቴ ከፍ አለ፤ እግዚአብሔር ስጸልይ የነበርኩባቸው ጊዜያት ሁሉ በራስ ወዳድነት የተሞሉ ከመሆናቸው የተነሳ ከንቱ መሆኑን ገለጠልኝ። አያችሁ እርሱ እንዲድን እኔ የፈለኩበት ዋነኛው ምክንያት እህቴ ጥሩ ባልዋን እንዳታጣ፣ ወንድና ሴት ልጆቹዋም አባታቸውን እንዳያጡ ነበር። ስለዚህ ነበር እግዚአብሔር ለእርሱ የምጸልየውን ጸሎት ሊመልስ ያልፈቀደው። የእኔ መነሻ አስተሳሰብ በሚስተካከልበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእርሱ የምጸልየውን ጸሎት መለሰልኝ።

በዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። ያዕቆብ 4፡3 እንዲህ ይላል "ትለምናላችሁ፤ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም።" ለአንድ ሰው (የቤተሰብ አባል ይሁን ጓደኛ) ለረጅም ጊዜ ውጤት ሳታይ የምትጸልይ ከሆነ መነሻ ሐሳብህ ምን እንደሆነ መመዘን አለብህ (በዋናነት ለእግዚአብሔር ክብር መሆኑን አረጋግጥ)።

በፍርድ ቤት ሂደት የተከሳሽ ጠበቃ በጉዳዩ ዙሪያ ጥያቄ ያነሳል፤ መከራከሪያ ነጥቦችን ያቀርባል፣ በጉዳዮቹም ዙሪያ ማስረጃ በማቅረብ ጉዳዩ ሕግን የጠበቀ

እንዳይደለ ያሳያል። ዳኛው ያመነ ከሆነ ጉዳዩ ሕግን ያልጠበቀ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋል፤ በመንፈሳዊው አለምም እንደዚሁ ነው። ለጠፉ ነፍሳት መጸሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦችንና ምክንያቶችን በመዘርዘር ከልባችን እንማልድ ይሆናል፤ መነሻ ሐሳባችን ግን ትክክል ካይደለ ሰይጣን ይቃወመናል። ከእግዚአብሔር ሐሳብ በመስማማት ጸሎታችንም ምልጃችንም ከንቱና ወና እንዳሆን ማድረግ አለብን። ትክክለኛ መነሻ ሐሳብ ከሌለን የምንጸልይለት ሰው ይሞትና ወደ ሲዖል የሚሄድ ይሆናል።

የምልጃ ሌላኛው ታማኝ ነገር ዋጋ የመክፈል መንፈስ ነው። ይህን ሐሳብ የሚደግፍ ተግባራዊ ክፍል በሮሜ 9፡3 ላይ ይገኛል፤ ጳውሎስ ለአይሁድ ወገኖች ደህንነት ሲል "እኔ የተረገምሁ ልሁን" ይላል። ሙሴም ለሕዝቡ ኃጢአትና በደል ሌላ አርባ ቀንና ሌሊት በጾም ጸሎት አድርጓል (ዘዳግም 9፡18-19)፤ አስቴር "እኔ ብጠፋም እጠፋለሁ" ብላ ነበር (አስቴር 4፡16)። በሴሚነሪ ማታው ፕሮግራም የግል ወንጌል ምስክርነት በሚል ሐሳብ በማስተምርበት ጊዜ የጸሎት ርዕሶችን የያዘ ካርድና በላዩ ላይ "ለአንተ ሲል ወደ ሲዖል እሄዳለሁ" የሚል ጽሑፍ ያለበት አዘጋጅቼ ነበር። ዋና ሐሳቡም እነርሱ ተጸልዮላቸው ባይድኑ ስለ እነርሱ ስንል ወደ ሲዖል ለመሄድ ፍቃደኛ መሆናችንን ትኩረት በመስጠት መጸለይ እንዳለብን ለማሳሰብ ነበር። በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎቼ የጸሎት ካርዱን ካደልኳቸው በኋላ መጋቢ የሆነው አንዱ እንዲህ አለኝ "እኔ ለማንም ብዬ ወደ ሲዖል ለመሄድ ፍቃደኛ ነኝ ብዬ አላስብም" በማለት ድምጹንም ከፍ አድርጎ ለሁላችን ተናገረ። በእርግጥ እግዚአብሔር በሌሎች ምትክ እኛ ወደ ሲዖል እንድንሄድ ባይፈልግም፣ ፈቃደኞች ከሆን ግን ጉዳዩ እኛ ስለሌሎች መጸለይ ያለብንን ጸሎት አበክረን በውጤታማነት እንድንጸልይ ያደርጋል።

ለሌሎች ነገሮች ሁሉ እኩል ቢሆኑም እንኳ ለጠፉ ነፍሳት በመጸለይ ህብረት በጣም ኃይለኛው ነገር ነው፤ ሁል ጊዜም አስቸኳይ ውጤትን ያስገኛል። የሚያጎላ መስተዋት የጸሐይ ጨረርን በአንድ ላይ በመሰብሰብ እሳት እንደሚፈጥር ሁሉ ክርስትያኖች ኅብረት በመፍጠር ለአንድ ለተወሰነ ሰው

የሚጸልዩ ከሆነ ኃይለኛው ይታሰራል፤ ደግሞም ትኩረቱ በሰውዬው ሕይወት በሚገለጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ይሆናል።
የዊልያም ኬሪ ልጅ ያቤጽ በምነጋገርበት ጊዜ የሆነው ይሄው ነበር። ይህም የሆነው የባብቲስት ቤተክርስቲያን ሚሶናዊያን በለንደን ከተማ ባደረጉት አመታዊ ስብሰባ ላይ ዶ/ር ሪላንድ ለያቤጽ ትልቅ ሸክም ተሰምቶአቸው እንዲህ ብለዋል፡- "ወንድሞቼ ለያቤጽ ኬሪ መዳንና መለወጥ አንድ የሆነ፤ አለምአቀፋዊ እና ጠንካራ የሆነ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር በዝምታ እናቅርብ። እንዲህ እንዳሉ ወዲያውም በጉባኤው መካከል መንፈስ ቅዱስ ሁለት ሺ በሚደርሱ የጉባኤ አባላት ላይ ወረደ። ከዚያም ሁሉንም በጸጥታ ወደ ተደረገ ምልጃ መራቸው። ወዲያውም አባት ኬሪ ከልጁ ያቤጽ መለወጡን የሚገልጽ ደብዳቤ ተቀበለ፤ ይህም ለውጥ የሆነው ጉባኤው እየጸለየ ባለበት በተመሳሳይ ሰዓት ነበር (ጎርዶን፣ 87-88)።
ጂም ሲምባል ለልጁ ኪርሲ ለሁለት አመታት ተኩል ምንም ውጤት ሳያይ ሳያቋርጥ ከባድ የጭንቅ ጸሎት አድርጓል። ማክሰኞ ማታ በነበረን የጸሎት ፕሮግራም በብሮክሊን ተበርናክል፤ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ ለኪርሲ መጸለይ እንዳለብን ተሰማት። በዚህም ሌሊት ቤተክርስቲያን ትልቅ የሥራ ክፍል ወደ መሆን ተቀየረች፤ በዚያም ኃይለኛ የሆነ የመቃተት ጸሎት "ሰይጣን አንተ ይህችን ልጅ በምንም ተአምር አታገኛትም፤ እጅህን ከእርሷ ላይ አንሳ እርሷ ወደ ጌታ ተመልሳለች" በማለት ጸለዩ። እንደ ጸሎቱ እንዲሁ እርሱዋ ከ32 ሰዓታት በኋላ ወደጌታ ተመለሰች (ሲይምባ ፣63-65)።
የኒው ሆፕ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን መጋቢው ሎዊስያና ለጉባኤው እነርሱ የሚያውቁትን ይህ ሰው እንዲለወጥ እፈልጋለሁ፣ ለእርሱ እጸልያለሁ የምትሉትን ሰው ስም ዝርዝር በወረቀት ላይ ጻፉ፤ ከተጻፉት አስራ ስምንት ሰዎች መካከል "ማይክ ዶሎስ" ብለው ጽፈው ነበር። እርሱም በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በሚያስገርም ሁኔታ ተለውጦ ጌታን ተቀበለ።
ለአሥራ ስምንት አመት ሙሉ ውጤት አልባ የሆነ ጸሎት ለባለቤቷ እንዲድን ስትጸልይ የነበረችው ሄሌን ግሬሻም መጋቢዋን ማይኪ ሐንዳንል በጸሎት እንዲያግዛት ጠየቀች። ሁለቱም በጋራ በመሆን ለባለቤቷ ሪኪ ሲጸልዩ ከሁለት

ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በአስደናቂ ሁኔታ ጌታን ተቀብሎ ተለወጠ። በእነዚህ በሁለት አመታት ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር ሕይወቱን እንደ መሐንዲስ እንዴት እንደቀየሰውና እንደቀየረው ምስክርነቱን ስትሰሙ በጣም ትገረማላችሁ። በሚገርም ሁኔታ ሚስቱና መጋቢው ለእርሱ እንደሚጸልዩ በፍጹም እርሱ አያውቅም ነበር።

እስቲ ለጠፉት አንድ ላይ በመሆን የተጠናከረና የሚያምር ጸሎት እናቅርብ፤ ለያቤጽ ኬሪ ሁለት ሺ የሚያህሉ ሰዎች አንድ ላይ ጸልየው በዚያች ሰአት ተለወጠ፤ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ለክሪሲ ሲምባል ጸለዩና እርሷ በ32 ሰአታት ውስጥ ንስሐ ገባች፤ ለማይክ ዶልስ ደግሞ አስራ ስምንት የሚያህሉ ሰዎች ጸልየው በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ተለወጠ። ለሪክ ጌርሻም ደግሞ ሁለት ሰዎች ጸልየው ከሁለት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በአስደቂ ሁኔታ ተለወጠ።

ስማ! አንተ ለምትወደው ሰው ካንተ ጋር በመሆን በጸሎት የሚያግዝ ሰው ብታገኝ በጣም አስገራሚ የሆነ ውጤት ታያለህ። በመንፈሳዊው አለም ሁለቱ አስር ሺ የሚያህሉትን ማሳደድ ይችላሉና (ዘዳግም 32፡30)፤ ሁለቱ ተስማምተው ቢቀርቡ በጸሎት ፈቃድ ሁሌም የጥያቄያቸውን መልስ ይቀበላሉ፣ ጌታ ራሱ እንዳለ (ማቴ 18፡19)!

የህብረት ጸሎት ለጠፉ ነፍሳት ኃይለኛ ለምን እንደሆነ ልግለጽላቸሁ። የመጀመሪያውና ዋናው እግዚአብሔር በሕዝቡ መሃል ለህብረት ትልቅ ዋጋ መስጠቱ ነው። ይህም ጌታ ኢየሱስ ለእኛ ባደረገው ጸሎት ውስጥ የሚገኝ መሻቱ ያለበት ማስረጃ ነው (ዮሐንስ 17) በዚህም ክፍል “እነርሱ አንድ ይሆኑ ዘንድ” በማለት አምስት ጊዜ ጸልዮዋል። በእግዚአብሔር ዘንድ እኛ ማድረግ ካለብን ዝርዝር ነገሮች የመጀመሪያው “ሁሉም ሰዎች ይድኑ ዘንድ ጸልዩ” የሚለው ነው (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-4)። ህብረት በጣም ውድ ስለሆነ፣ የሚማልዱም በጣም ውድ ስለሆኑ (እግዚአብሔር በእስራኤል አንድ እንኳ ስላላገኝ፣ ኢሳይያስ 59፡16)፣ እነዚህን ሁለቱን ማለትም ህብረትንና ምልጃን አንድ ላይ ስታደርግ በእጥፍ ውድ የሆነ ነገር ትፈጥራለህ። እግዚአብሔርም

በጣም ደስ ብሎታልና ውድ ሆኖ ያገኘዋል፣ እኛ ከምናስበውም ከምንገምተውም በላይ ይባርከናል።
ሁለተኛው ምክንያት በጣም ቀላል ነው፦ የሰውን ሕይወት የሚቆጣጠር አንድ ሐይለኛ ሰው ብቻ አለ። ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ወደዚህ አንድ ሐይለኛ በጋራ በመቃወም ሲመጡ በቀላሉ ይሸነፋል፤ ምክንያቱም በዮሐንስ 4፡3-4 "በአለም ካለው ይልቅ በእኛ ያለው ይበልጣል" ተብሏል። ከዚያ በኃላ በቤቱ ውስጥ ያለውን ንብረት መመዝበር በጣም ቀላል ይሆናል። ብዙውን ጊዜ የጠፉ ነፍሳት ወደ አንተ እርዳታ ፈልገው ይመጣሉ። ለጂምቦ ባሬቲኔ የሆነው ይሔው ነበር። እኔ ከአምስቱ ጋር አብረን ልንጸልይ ቃል ኪዳን አደረግሁ። ከሁለት ወራትም በኃላ በጣም በኃይለኛ የመንፈስ ወቀሳ ውስጥ ሆኖ እኔን ፍለጋ ወደ ቢሮዬ መጣ። በዚያ ጊዜ ይህን ትምህርት በማስተማር በአርካንሳ የጸሎት ኮንፍራንስ ላይ ነበርኩኝ። ስለዚህ እኔን ስላጣ በቤተክርስቲያናችን ወዳለበት ወደ አንድ ሰባኪ ቤት የመዳንን መንገድ በመፈለግ ሄደ፤ ለመዳን እኔንመጠበቅ የለበትም ምክንያቱም ባለበት ሆኖ በዚያ ሰዓት መዳን ይችላልና።
ሶስተኛው ምክንያት ትዕቢት ስለተወገደ ነው። እግዚአብሔር ምስጋናን እንደሚወድ እንዲሁ ሰይጣን ትዕቢትን ይወዳል። ስለዚህ አንድ ሰው ትሑት ሆኖ የጸሎት እርዳታ ማድረግን እስከሚለማመድ ድረስ ሰይጣን ሁል ጊዜ ሁኔታዎችን ይቆጣጠራል። ከዚሁ ጎን ለጎን እግዚአብሔር ራሱ "ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል" (ያዕቆብ 4፡6)። በተለያዩ ጊዜያት እኔ ለጠፉ ባሎች በምመሰክርበት ጊዜ ሚስቶች ስለዚህ ጥሩ ነገር ለእኔ መንገር ይጀምራሉ። የእነርሱም ትዕቢት በእግዚአብሔር ፊት የእርሱን ሁኔታ እንዲቀበል አያደርጋትም። በሚያሳዝን ሁኔታ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሚስቶች ባሎቻቸውን ለክርስቶስ መቼም ማርኬ አላውቅም።

# ምዕራፍ 4

# ዝርዝር የጸሎት ጥያቄዎች

አብዛኛዎቻችን አንዳንድ ሰዎች እንዲድኑ በምንጸልይበት ጊዜ ከባድ ሁኔታ ያጋጥመናል፤ ምክንያቱም እኛ ማድረግ የምናውቀው "እግዚአብሔር ሆይ እነ እገሌን አድን" የሚለውን ነው። ይህንን አንድ ሐረግ በመደጋገም እንደ ሞኝ እንጸልያለን፤ ከዚህ የተነሳ ብዙውን ጊዜ ይሰለቸንና ጸሎቱን እናቋርጣለን። ይሁን እንጂ እንዲህ አይነቱ ጸሎት አራት ነገሮችን ያካትታል፦ ግለሰቡን፤ የጠፋውን ነፍስ የሚያድነውን፤ የእግዚአብሔርን ቃልና መነቃቃት። በእነዚህ ነገሮች ዙሪያ በዝርዝር መጸለይን በምንማርበት ጊዜ ምልጃችን ተግዳሮት የተሞላውና ውጤታማ ይሆናል።

ለግለሰቦች በስም በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወቱ አምስት ነገሮችን እንዲሰራ እንጠይቃለን። በመጀመሪያ እግዚእብሔር እንዲቀድሰው እንለምናለን። ይህ ሐሳብ ሊያስገርመን የሚችል ቢሆንም፣ እግዚአብሔር የማዳንን ሥራ በእያንዳንዱ ሕይወት ሲጀምር የሚሰራው ስራ ይሄንኑን ነው። እርሱ ሰውየውን ከማዳኑ በፊት ሁል ጊዜ ይቀድሰዋል ይለየዋልም።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልጽ ሲያስተምር በ2ኛ ጴጥሮሰ 1፡2 እንዲህ ይላል "የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፤ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ"። በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-14 "እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኃልና"። እግዚአብሔር በሰውዬው ዙሪያ አላማ ካደረገ በኋላ በሰውየው ሕይወት ተጽዕኖ ማድረግን ወዲያው ይጀምራል። ስለዚህ በዚህ ሰው ላይ በመገረም ትልቅ ተጽዕኖ ያደረጋል። እግዚአብሔርም ራሱ በሰውየው ውስጥ በሚገኝበት ጊዜ ከእዕምሮ በላይ የሆኑ ነገሮች መሆን ይጀምራሉ። ይህንንም በዚህ መጸሐፍ መጨረሻ ላይ የግል የሕይወት ምስክርነቶችን ስታነብ ማስተዋል ትችላለህ።

ይህ አስደናቂ እውነት ለሌሎች ለምንጸልይ ለእኛ ትልቅ ማበረታቻ ነው፤ ምክንያቱም የመከሩ ጌታና ባለቤት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ ይሄንን ሰው ስለሚያገኘው እርግጠኛ ሆነን በእርሱ መታመን እንችላለን። ከሃዲ እንደሚሆን እየተናገረ የቆየ አንድ የኮሌጅ ተማሪ አንድ ጊዜ ለሲ ኤስ ሌዊስ በጻፈው ጽሑፍ እንዲ ብሎ ያብራራ ነበር፡- "ከእኔ ጋር ሆነው ስለ እምነታቸው ይመሰክሩ ከነበሩት አንዳንድ ክርስቲያኖች ጋር ነበርኩ። እነርሱ የተናገሩት አንዳንድ ነገሮች ለአዕምሮዬ ዕረፍት አልሰጠኝም። ከዚህ የተነሳ በትልቅ ትግል ውስጥ ነበር ያሳለፍኩት። ዶ/ር ሌዊስ ምን ነበር ያሰበው? ሌውስ ለእርሱ እንዲህ ሲል የመልስ ጽሑፍ ላከለት 'ይመስለኛል አንተ

በማጥመጃ መረብ ውስጥ ነህ፤ መንፈስ ቅዱስ በአንተ አጠገብ ነው፣ ማምለጥ የምትችል አይመስለኝም” (ዳን ፣118)።

ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን “መከሩን” እንዲሰበስቡ በላካቸው ጊዜ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ነበር የሰጣቸው “መጀመሪያ ለዚህ ቤት ሰላም ይሁን በሉ” (ሉቃስ 10፡1-5)፣ ሁሌም ቢሆን የእግዚአብሔር ምስራች ወንጌል ሰዎችን ወደ ንስሐ ይመራል (ሮሜ 2፡4)፤ እግዚአብሔር ነጻ በማውጣት እንዲባርካቸው መጠየቅ አለብን። አንዳንድ ጊዜ ለሌሎች የምንጸልየው የደህንነት ጸሎት በቶሎ ምላሽ የሚያመጣ ከሆነ እንረበሻለን፤ ትዕግሥትም እናጣለን። በዚህም እግዚአብሔር መከራ በመላክ እንዲያስተምራቸው በሚስጥር የምንለምንበት ጊዜ አለ። ሰማርያ የተወሰነ አካባቢ መንደሮች ጌታ ኢየሱስን ለመቀበል እምቢ ባሉ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ እግዚአብሔር ከሰማይ እሳት ልኮ እንዲያቃጥላቸው ጠይቀው ነበር። ይሁን እንጂ እርሱ እንዲህ ሲል ገሰጻቸው “ምን አይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም” (ሉቃስ 9፡55-56)። ውዱ አዳኛችን በይበልጥ እንዲሰራ ከፈለግን ዘወትር ለሕዝቡ እግዚአብሔር መልካም ነገር እንዲሆን መመኘት አለብን። የምንጸልይላቸው ሰዎች የእግዚአብሔር ልዩ በረከት በእነርሱ ላይ እንዲሆን ለየት አድርገን መጠየቅ አለብን።

በሶስተኛ ደረጃ ወቀሳ ለደህንነት ሙሉ በሙሉ አስፈላጊ ስለሆነ ጌታ ግለሰቦችን እንዲወቅሳቸው እንጠይቃለን። መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው አንድን ሰው ወደ ማመን የሚያመጣው፤ ስለሆንም በጸሎታችን ዮሐንስ 16፡8-11 ያለውን ሐሳብ በመጥቀስ መማለድ አለብን። መውቀስ ማለት መሰረታዊ ሐሳቡ ስህተትን እንዲያምን ማድረግ ነው። የጠፋው ነፍስ ትልቁ ችግር ወይም ስህተት “በጌታ ኢየሱስ አለማመን” ሲሆን፣ ይሄ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የሚወቅሰው ኃጢአት ነው (ዮሐንስ 16፡9)።

ሰዎች የራሳቸውን ኃጢአት ሁሉ ያውቃሉ ግን አንድ የማያውቁት ኃጢአት በጌታ ኢየሱስ አለማመናቸውን ነው። ይሄ ኃጢአት ብቻውን ሰዎችን ወደ ሲዖል የሚመራ ስለሆነ ሰይጣን ሰዎችን በእውርነት ያቆያቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ የጠፋው ሰው መዳን ይችል ዘንድ ኢየሱስን በክብሩ በመግለጥ ይወቅሳል፤ ያሳምናል። እዚህ ላይ ወቀሳ ተደርጎል ማለት ደህንነቱ ወዲያውኑ ተረጋግጧል ማለት እንዳልሆነ ግን መዘንጋት የለበትም። ጳውሎስ በሐዋሪያት ሥራ 24፡25 “እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለመግዛት ስለሚመጣውም ኩነኔ ሲነጋገር ሳለ፤ ፊልክስ መፍራቱን ወይም መወቀሱን” ይናገራል፤ ሆኖም እርሱ ደህንነት አግኝቶአል ለማለት አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልከታ የለም።

በመቀጠልም ጌታ አዕምሮውን ለእውነት እንዲከፍት እንጠይቃለን። አንድ ሰው ደህንነት ማግኘት እንዳለበት ተወቅሶ ወደ ማመን ከመጣ በኃላም፣ በጨለማ

የተዋጠው አዕምሮ ለታላቁ ክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በመንፈሳዊው ጨለማ አለም አማካኝነት የተዘጋ ሊሆን ይችል ይሆናል (2ኛ ቆሮንቶስ 4:6)። አንድ ጊዜ አዕምሮና ልብ ለእውነት የተከፈተ ከሆነ፣ ለእርሱ ወንጌልን እንዲናገሩ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ይጠቀማል። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለእውነት መሻቱ ቢኖረው፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለአምልኮ ቢመጣ፣ መጽሐፍም በእጁ ቢኖር እንኳ "የሚመራኝ አንድ ሰው ሳይኖረኝ እንዴት ልረዳ እችላለሁ" በማለት መረዳት አለመቻሉን በግልጽ ተናገረ። (ሐዋ 8:26-39)።
የቆርነሌዎስ ታሪክ ደግሞ በጣም አስገራሚ ነው (የሐዋሪያት ሥራ 10)። እርሱ "ከቤተሰቡ ጭምር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ፤ ለድሆች ምጽዋትን የሚሰጥና ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ" ሰው ነበር። እርሱ እኛ ከምናውቃቸው ብዙ ክርስቲያኖች የተሻለ ሆኖ ሳለ የጠፋ ነበር። ምክንያቱም የደህንነትን መንገድ አልተረዳም ነበር። በመልአኩም አማካይነት "ምን ማድረግ እንደሚገባው" በጴጥሮስ በኩል መልዕክት እንዲላክለት ሆነ። ቆርኔሌዎስና አብረው የነበሩ ሁሉ ለወንጌል በጣም ክፍት ከመሆናቸው የተነሳ ቃሉን እንደ ሰሙ ጴጥሮስ እየሰበከ ሳለ፣ ወዲያው መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ላይ ወረደና ወዲያው ዳኑ።
እግዚአብሔር የጠፉ ነፍሳትን ልብና አዕምሮ እንዲከፍት ጠይቁት፣ እርሱም ያደርገዋል፤ እነርሱንም በሚያስደንቅ ሁኔታ ይድናል! እግዚአብሔር እንዲያድናቸው ለድነትም የሚጋብዝ ማኛውም ነገር እንዲያደርግ መጠየቅ ይኖርብናል። የሕይወትን አቅጣጫ በመቀየር ወደ ንስሃ የሚያመጣው እርሱ ብቻ ነው። በሉቃስ 19:10 ላይ "የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው" በሚለው ክፍል ላይ ቻፌር ሐሳብ ሲስጥ እንዲህ ይላል፡- "የጠፉትን ማዳን ከሙከራ የዘለለ ወይም የበለጠ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ በሁሉም እጅ አሉና። ያልዳኑትን ወደ ደህንነት ያመጣ ዘንድ አስፈላጊውን ሁኔታ በማመቻቸት መለኮት ያስተካክላል (ቻፌር፣ 3-4)።
የቶኒ ፌንቶንት ቤቴሰብ እርሱ በጌታ ኢየሱስ እንዲያምን ለብዙ አመታት ጸልየው ነበር። ጸሎታቸውም እስከ ሚያዚያ 22,1982 ድረስ ዋጋ ያልነበረው ይመስል ነበር። በዚህ ዕለት ግን እርሱ የአውሮፕላን አደጋ ደርሶበት ከሞት አፋፍ በጥቂቱ ተረፈ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ያለው አመለካከት ተቀየረ፣ ቀሪ ዘመኑም ቀላል ሆነ።
አንድ ሰው ወንጌልን ለመቀበል የተዘጋጀ ከሆነ፣ ለዚያ ሰው የሚመሰክር ሰው ሊኖር ይገባል። ስለዚህ ዋናው ነገር መሆን ያለበት እግዚአብሔር ለዚህ ሰው ወንጌልን የሚመሰክርለት ሰው እንዲልክ መጸለይ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህን እንድናደርግ ነው እግዚአብሔር የሚያዘን "መከሩ ብዙ ነው፤ ነገር ግን ሰራተኞቹ ጥቂት ናቸው። ስለዚህ የመከሩ ጌታ የመከሩ ሰራተኞችን እንዲልክ ጸልዩ" (ማቴዎስ 9:37-38)። ሰራተኞች ጥቂት ማለትም በመጠን፣ በቁጥር፣

በጊዜ፣ ወይም በዋጋ (የእስትሮንግ መዝገበ ቃላት እንዳስቀመጠው) ትንሽ ስለሆኑ በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር እርዳታ እንዲሆን መጸለይ አለብን። ወደ እርሱ መጸለይ ያለብንም መጀመሪያ ብዙ ሰራተኞችን እንዲልክ ነው። የግሪኩ ቃል "እካባሎ"፡- ጉልበትን መጠቀም የሚለውን ሐሳብ ያመለክታል (ለማውጣት፣ ለመወርወር፣ ለማድቀቅ የሚሆን ጉልበት እንደማለት ነው )።

እግዚአብሔር ዮናስ ወደ ነነዌ ሄዶ ቃሉን እንዲሰብክ በላከው ጊዜ አልሄድም ብሎ እንዳስቸገረው ታስታውሳለህ? እግዚአብሔር እርሱ እንዲሄድ በቀጥታ "አስገድዶት" ነበር። የዚህ አይነት ተመሳሳይ ሁኔታ ቤተክርስቲያን በራሷ ክልል ካለችበት አመቺ ሁኔታ ወጥታ ወንጌልን በምትሰብክበት ጊዜ አጋጥሞአታል። እግዚአብሔር ታላቅ ስደት እንዲሆን ፈቅዶ ነበር፤ "በዚያን ቀን በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፣ ሁሉም ከሐዋርያት በቀር ወደ ይሁዳን ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ (የሐዋሪያት ሥራ 8፡1)። ነገር ግን "የተበተኑት ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡4)።

ሰራተኞች ጥቂት መሆናቸው በቁጥር ብቻ ሳይሆን፣ በጊዜና በዋጋ ረገድ ትንሽ በመሆናቸው ጌታ አስፈላጊ በሆነው ሁሉ ብቃትና ውጤት እንዲሰጣቸው መጸለይ አለብን። ይህም ሁሉ ብቃት የሚመጣው ከውዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ሳሙኤል ቼድውክ እንዲህ ይላል "የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ከስዕብናው የተለየ አይደለም፤ እግዚአብሔር ባሕርያቱን አያጠፋም፤ ኃይሉ የሚከራይ አይደለም። ከስብዕናው ልለይ አልችልም። እርሱ ኃይል ሰጪ ብቻ አይደለም፤ ማንም ይህን ማድረግ አይችልም" (ቻድውክ፣ 89)።

ለዚህም ነበር ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ያዘዘው (የሐዋሪያት ሥራ 1፡4-5)። "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፤ በሰማሪያ እስከ ምድር ዳር ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ" (የሐዋሪያት ሥራ 1፡8)።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የልጅነት መብታችን ነው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38-39)። ቤተክርስቲያን በአጠቃላይ ስለ እርሱ የምታውቀው ጥቂት ነው፤ ምክንያቱም ኤፌሶን 1፡19 "በቅዱሳን ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ" ይላልና! እኛ ሁላችን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመሞላት እነርሱን ማስቆም ስላልቻልን በዙሪያችን ያሉ ብዙ ነፍሳት ተንደርድረው ወደ ሲዖል እየሄዱ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የእርሱን ሰራተኞች በመንፈሱ እንዲሞላ፤ በኃይል፣ በብቃትና ድፍረት እንዲሞላ መጸለይ አለብን (የሐዋሪያት ሥራ 4፡31)። ጥበብ (ምሳሌ 11፡30)፤ ቅንአት (ቆላስይስ 4፡12-

13)፤ ርህራሄ (ይሁዳ፣ 22-23)፤ መለኮታዊ እይታ (ኤርሚያስ 33፤3) እናም ነፍሳት ይድኑ ዘንድ!!!

ሰዎች እንዲድኑ ሰራተኞችም ደግሞ ለእነርሱ እንዲመሰክሩ ከጸለይን በኃላ አሁን ደግሞ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ቃል ይነገር ዘንድ እንጸልያለን። ምክንያቶቹን በሁለት መልክ መረዳት ይቻላል፦ በመጀመሪያ ማንም የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሰማ መዳን አይችልም (ሮሜ 10፡14)፤ ሁለተኛው ሰይጣን የእግዚአብሔር ቃል ይጠላል። ከዚህም የተነሳ በምችለው አቅምና ኃይል ሁሉ ምንግዜም በመቃወም ሰዎች ቃሉን እንዳይሰሙና እንዳይቀበሉ ያደርጋል። አንድ ሰውን ለማሳመን (የሐዋሪያት ሥራ 2፡37)፣ ነጻ ለማውጣት (ዮሐንስ 8፡32)፣ ዳግም ልደት ወይም ድነት ለመስጠት (1ኛ ጴጥሮስ 1፡23) የእግዚአብሔር ቃል ጉልበት አለው። ሰይጣን በማጥፋት (ሉቃስ 8፡11-15)፣ በማፍረስ (2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4-5) እና በማታለል (2ቆሮንቶስ 11፡3-4) ይህን ኃይል ይቃወማል። ለኃይለኛ ሰው ብዙኃን እንደሚሆኑት ያህል የእግዚአብሔር ቃል ለሰይጣን እንዲሁ ነው። እርሱ መከላከል እንዳይችልና አቅም የለሽ እንዲሆን ያደርገዋል። ምርኮኞቹ የሆኑትን ነጻ በማውጣት መንግሥቱን ያዳክማል፤ "እውነትን ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኃል" (ዮሐ 8፡32)። በዚህ ጊዜ መታሰብ ያለበት የተነገረልህ እውነት ሳይሆን ነጻ የሚያወጣህ፣ ያወከው ወይም የተቀበልከው እውነት ነው። ስለዚህ ሰዎች እውነቱን እንዲያውቁ የሚችለውን ማድረግ ይኖርብናል።

ለደቀመዛሙርት የዘሪውን ምሳሌ ሲያብራራ ሰይጣን ወዲያው መጥቶ፣ ሰውየው ቃሉን መረዳት ከመጀመሩ በፊት እንደሚሰርቀው (ማርቆስ 4፡15) ተናግሯል። ለጠፉ ነፍሳት ሰለምንናገረው የእግዚአብሔር ቃል መጸለይ አለብን። ቃሉን ተጠቅመን እግዚአብሔር የጠፉትን እንዲለውጥ ስንጸልይ አምስት የተለያዩ ጥያቄዎችን እናቀርባለን። በመጀመሪያ ቃሉ ነጻ ሆኖ ወደ እነርሱ እንዲደርስ ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡1፤ በሌላ አገላለጽ በምንም መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ፍሰት ሰይጣን እንዳይከለክል ማድረግ ነው። እርሱ በሚችለው መንገድ ሁሉ ለማስቆም ይፈልጋል፤ ቃሉ እንዳይደርስ ከመከልከልና ከማበላሸት በተጨማሪ ቃሉን ማጣመም፤ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱሶችን ማቃጠል፤ በቃሉ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር ማድረግ እና ወዘተ። ቀጥሎ የእግዚአብሔር ቃል እንዲከበር እንጸልያለን (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡1)፤ ይህም ቃሉ በሚሰሙት ዘንድ በደንብ እንዲከበር ዋጋ ይሰጥ ዘንድ ነው። በመዝሙር 138፡2 ላይ የተጻፈውን "ከስሞች ሁሉ በላይ ቃሉን አክብሩ" የሚለውን ስናይ ለቃሉ ለየት ያለ አዲስ አክብሮት እንሰጣለን። በእርግጥ እግዚአብሔር ራሱ ሥጋ ለብሶ ገልጧል። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃሉም እግዚአብሔር ነበር፤ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በመካከላችን አደረ" (ዮሐንስ 1፡1፤14)። የእግዚአብሔር ቃል

እንዲበዛ እንጸልያለን (የሐዋሪያት ሥራ 12፡24)። የማጨድ አንዱ ሕግ "በልግስና የሚዘራ በልግስና ያጭዳል" (2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6) የሚል ነው። የእግዚአብሔር ቃል በኃይል እንዲገለጥና እንዲሰራ እንጸልያለን (የሐዋሪያት ሥራ 19፡20)። አንድ ዘር በሲሚንቶ ውስጥ ተቀብራ ማደግ ስትጀምር በውስጧ የዘር ሕይወት ከመኖሩ የተነሳ ሲሚንቶውን ፈንቅላ እንደምትወጣ ሁሉ በልብ ውስጥ የተተከለ የእግዚአብሔርም ቃል እንዲሁ ነው። ለቃሉ በመጸለይ እኔን ደስ የሚለኝ ጸሎት ቃሉ ውጤታማ እንዲሆን የሚለው ነው። የሐዋሪያት ሥራ 14፡1 "እነርሱ ተናገሩ ብዙ ሕዝብም ከአይሁድና ከግሪክ የሆኑ ቃሉን አመኑ" ያላል። በኢሳያስ 55፡11 ላይ ያለው ሐሳብ ተግባራዊ እንዲሆን መማጸን አለብን፡- "ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል፤ የሚሻውን ያደርጋል፣ የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" እግዚአብሔር ቃሉ ውጤታማ እንዲሆን ይፈልጋል። ስለዚህ እርሱ ውጤታማ እንዲያደርግ ጸልይ፤ ምክንያቱም ይህ መለኮታዊ ፈቃዱ ነው፤ ጸሎትህም ይመለሳል።

እኔ አንድ ነገር ልንገራችሁ የአስቆሮቱ ይሁዳ ከቃሉ ጋር ቅርብ፣ ተደጋጋሚ ቆይታና ግንኙነት የነበረው ሰው ነው። ነገር ግን ሞቶ ወደ ሲዖል ሄዷል። ኢየሱስም እንዲህ ነበር ያለው "ለእርሱ ባይወለድ ይሻለው ነበር" (ማርቆስ 14፡21)። ፈሪሳዊያን በዘመኑ ታዋቂ ሐይማኖቶኞች ነገር ግን ቃሉን በግብዝነት የተላበሱ ነበሩ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል መጥቀስ ቢችልም ከእግዚአብሔር መንግሥት በብዙ የራቁ ናቸው። ማስታወስ ያለብን አንድ ነገር አንድ ሰው መዳን የሚችለው በልቡ የተዘራው ዘር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቅስቀሳ ሲደረግለት ነው። ለዚህም ነው ቃሉ በሚሰሙ ሰዎች ዘንድ ውጤታማ መሆን እንዲችል መጸለይ ያለብን።

ብዙዎች ሲድኑ ማየት የምንፈልግ ከሆነ ለመነቃቃት መጸለይ አለብን። በመነቃቃት ዙሪያ ታዋቂ የሆነው ክፍል እንዲህ ሲል ይጀምራል፡- "በስሜ የተጠሩ ሕዝቤ ራሳቸውን አዋርደው ቢጸልዩ" (2ኛ ዜና 7፡14)፤ በዚህ ስፍራ የተጸለየው ጸሎት የምልጃ (ለሌሎች የሚደረግ ጸሎት) ነው። ኢዮብ ለጓደኞቹ ከጸለየ (በዕብራይስጥ በላይ ያለው ክፍል ከተጠቀሰው ቃል ጋር አንድ ነው) በኋላ ነበር፣ እግዚአብሔር የእርሱን ሁኔታ የቀያየረው (ኢዮብ 42፡10)። በመነቃቃት ወቅት አብዛኛው ጸሎት ለሌሎች መጸለይን ያካተተ አይደለም። ዱንካን ካምፕቤል መነቃቃትን "ሰዎች በእግዚአብሔር ረክተው ሲቀሩ" በሚለው ሐሳብ ያብራራል (ኤድዋርድስ፣ 26)። ሰዎች በእግዚአብሔር ሲረኩ ለራሳቸው ከማሰብ ይልቅ ለሌሎች ያስባሉ። እግዚአብሔር ለነፍሳት ያለው ሸክም የእነርሱም ይሆናል።

በመነቃቃት ጊዜ ስላለው የጸሎት ኃይልና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ፋይኒ ምን ብሎ እንደሚያብራራ እንመልከት፡- "ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሜ ተናግሬአለሁ።

በእነዚህ መነቃቃት በሚፈጥሩ ሰዎች ውስጥ ያለው መንፈስ የእነርሱን ሁኔታ በደንብ ያሳያል። ይህንን ተመሳሳይ አይነት ነገር በጸሎት አዲስ በተለወጡ ለጋ አማኞች መከናወን አለበት። እነርሱም አንዳንድ ጊዜ በተደጋጋሚ ሌሊቱን ሙሉ ሰውነታቸው እስኪዝል ድረስ ሊጸልዩ ይችላሉ፤ ይህን የሚያደርጉት በዙሪያቸው ላሉቱ ላልዳኑ ነፍሳት ነው። በክርስቲያኖች አዕምሮ ትልቅ የመንፈስ ቅዱስ ግፊት ኃይል አለ፤ እርሱም ከእነርሱ ጋር በመሆን ለሚጠፉ ነፍሳት ሸክሙን ይጋራል። ክርስቲያኖች በሚሰባሰቡበት በብዙ ቦታ ንግግር ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ በጉልበታቸው ተንበርክከው ሲጸልዩ በአብዛኛው ይታያል። የጸሎት ስብሰባዎች ብቻ አይደሉም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታየባቸው፣ ድብቅ የሆኑ ጸሎቶችም ጭምር እንጂ! ክርስቲያኖች ጸሎትን ትልቅ ጉዳይ ማድረግ አለባቸው፤ አንዳንዶች በግል ጸሎታቸው ለሰዓታት ቆይተዋል። ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ሆነው ተስፋውን ተቀብለውታል “ከእናንተ ሁለቱ በምድር የሚስማሙ ከሆነ፣ የሆነ ነገርን እንደመንካት በሰማይ ያለው አባቴ ለእነርሱ ያደርጋል። አንዳንድ ሰዎችንም የጸሎት ርዕስ ያደርጋል፤ እነርሱም ትልቅ ዋጋ መክፈላቸው አስደናቂ ነው። በሁሉም አቅጣጫ የጸሎት መልሶች በዝተው ተገልጠዋል። በዚህም እግዚአብሔር በየዕለቱና በየሰአታቱ ጸሎትን እንደሚመልስ ከማመን ማንም ምክንያት ማቅረብ አይችልም” (ፊኔይ፣ 141-42)። ስለ መነቃቃት የተጻፉትን በጥንቃቄ ማንበብ በመቶዎች፤ ሺዎችና ሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የተለወጡት በመነቃቃት ጊዜ እንደሆነ ነው። ጆናታን ኤድዋርድም የተረዳው እግዚአብሔር መነቃቃትን በዋናነት በመጠቀም መንግሥቱን እንደሚያስፋፋ ነው (ኤድዋርድ፣ 26)። ነፍሳት ሲድኑ ማየት ከፈለክ ለመነቃቃት ጸልይ!

# ምዕራፍ 5
# መንፈሳዊ ውጊያ

ለጠፉት በምንጸልይበት ጊዜ ተቀዳሚ አላማችን እግዚአብሔር እነርሱን እንዲያድናቸው ማሳመን አይደለም፤ 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 "እርሱ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም" ይላልና! ለአለም ኃጢአት ሁሉ እንዲሞት የላከውም ለዚሁ ነውና (1ኛ ዮሐንስ 2፡2)። ለሌሎች መጸለይ መንፈሳዊ ውጊያ ስላለበት ከሰይጣን ተጽዕኖ ነጻ መውጣትን ይጠይቃል።

እውነትን ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ስላለበት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚገልጸውን አጠር ያለ ማብራሪያ መመልከት ያሻል። የጠፉ ሰዎች ሰይጣን ነጻ እንዲወጡ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አስሮ የያዛቸው (ኢሳያስ 14፡17) ፣ በሰይጣን አገዛዝና ሕግ ሥር ያሉ ባሪያዎች (የሐዋሪያት 26፡18)፣ የሰይጣን ልጆች (ዮሐንስ 8፡44)፣ ለወንጌል (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡3-4)፣ በሰይጣን ኃይል የተሞሉ (ኤፌሶን 2፡2)፣ ተስፋ በማጣት በሰይጣን እጅ ውስጥ የተያዙ (1ኛ ዮሐንስ 5፡19) እንዲሁም በኃይለኛው ቤት ውስጥ ያሉ ናቸው (ማርቆስ 3፡27)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ ተንተን በማድረግ ሙሉ ሥዕሉን በሙላት እንድናይ ያግዛሉ። ለምሳሌ፡- ኤፌሶን 2፡2 "በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም በዚህ አለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሰራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፤ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። "በግሪኩ "ኢነርጎ" የሚል ሲሆን ትርጓሜው "ኃይል መስጠት" ማለት ነው። ምልከታውም በቀጥታ የጠፉ ነፍሳት በዲያብሎስ መንፈስ ተሞልተዋል የሚል ነው። በርግጥ የጠፋው ሰው ይህን አይረዳም፣ አያውቅም፤ እውነት ነው ብሎ መቀበልም አይችልም። እርሱ የሚያስበው ነጻ እንደሆነ ነው (ማለትም መጥፋቱ) ፤ ሥራው በአየር ላይ በሚሰለጥነው አለቃ መንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆኑን ነው" (ዱን፣ 120)።

1ኛ ዮሐንስ 5፡19 ስንመለከት "ከእግዚአብሔር እንደሆንን ዓለም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን" ። መላው አለም (በውስጧ ያሉ ፍጥረታት ጭምር) ከዚህ ከክፉው ተጽዕኖ ሥር ድካም ወድቀዋል ማለት ነው። "prostrate" አደከመ የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው የዌብስተር መዝገበ ቃላት "በአንድ ነገር ቁጥጥር ስር በመሆን ፊት ለፊት በተገዥነት መውደቅ" እንደሆነ

ያብራራል። ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ በተመለከተ ጆን እስቶት አለም “በክፉ ቁጥጥር ስር ያለች (የተኛች)፣ ለመነሳትና ነጻ ለመውጣት ምንም ትግል የማታደርግ፣ በሰይጣን ክንድ ላይ መተኛቷ የማታውቅ ናት” ይላሉ (እስቶት፣ 193)።

የጠፉትን ለክርስቶስ በመማረክ ረገድ ማርቆስ 3፡27 በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉ ሌሎች ክፍሎች ይልቅ በጣም አሰፍላጊው ነው ብዬ አስባለሁ። በዚህ ክፍል ኢየሱስ ራሱእንዲህ ይላል፡- “ነገር ግን አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለም፤ ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።” የጠፋ ሰው በቁጥጥር ሥር ካለበት ከሰይጣን ተጽዕኖ እንዲወጣ ነጻ የሚያወጣው ሌላ ሰው ከሌለ በስተቀር የማይቻል ነው፤ ነጻ የማውጣት ሥራ ተግባራዊ የሚሆነው በጸሎት ነውና።

የነፍሳት ጦርነት ድል ለማግኘት ማድረግ ያለብን አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ የመጀመሪያው እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን የጦር መሣሪያ መጠቀም ነው። በወታደራዊ ሥልጠናዬ ክፍል አንዱ ስራ መሳሪያን መጠቀም ስለነበር፣ በቬትናም ጦርነት እጅጉን ጠቅሞኛል። ኤም 16 ከሚባለው መሳሪያ ጋር ብዙ ልምድ ስለነበረኝ መብራት ሳይኖር በጨለማ እንኳ መፍታትና መግጠም እችል ነበር፤ ይህ መሳሪያ በውጊያ ሜዳ ሕይወትን ለማዳን በእጅጉ አግዞኛል።

በመንፈሳዊ ውጊያ ወቅት የምንጠቀማቸውን ኃይለኛ የውጊያ መሣሪያዎች እግዚአብሔር አዘጋጅቶልናል። “የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፤ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው” (2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4)፤ የእኛ ችግር ከውጊያ መሳሪያ፣ ከራሱ ከውጊያው ጋር ምንም አይነት ትውውቅ አለማድረግ ነው።

የውጊያ መሳሪያዎቻችሁና አጠቃቀማችሁን ከማስተዋወቅ በፊት ዋናውና ትልቁ የጦር መሳሪያ ጸሎት ነው፤ በጸሎት ነው የምንዋጋው! ወንድሜ ሚኬይ ቦኔር ብዙውን ጊዜ ሁሉም ጸሎት ውጊያ ነው ሲል ሰምቸዋለሁ። በማንጸልይበት ጊዜ ሰይጣን እያሸነፈን እንደሆነ ይታወቃል። ይሁን እንጂ እኛ በምንጸልይበት ጊዜ እርሱ እየተሸነፈ ነው፣ ጸሎትን ማቆም የምንችልበት ኃይል የለም። እግዚአብሔር “ሳናቋርጥ እንድንጸልይ” የሚያሳስበው ለዚሁ ነው (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17)። ሐዋሪያት ሳይቋርጡ ለጸሎትና ቃሉ አገልግሎት

ራሳቸውን የሰጡበት ምክንያትም ይሄው ነው (የሐዋሪያት ሥራ 6፡4)። ሁሉም የውጊያ መሳሪያ ማለትም ታንክ፤ ቦምብ፤ ሚሳኤል፤ ክላሽ ወዘተ… ጠላትን ድል ለማድረግ አንድ አላማ ይውላሉ፤ ሁሉም መንፈሳዊ የውጊያ መሳሪያዎች ተመሳሳይ አላማ ለማስፈጸም ጥቅም አላቸው። ኃይለኛ ከሆኑ መንፈሳዊ የጦር መሳሪያዎች ጋር እንተዋወቅ፣ በጸሎታችንም ጊዜ እንጠቀምባቸው።

የክርስቶስ ደም አንዱ ኃይለኛው የውጊያ መሳሪያችን ነው። ራዕይ 12፡11 እንዲህ ይላል "እነርሱ ከበጉ ደም የተነሳ ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት፤ ነፍሳቸውንም እስከሞት ድረስ አልወደዱም"። ዕብራውያን 2፡14 የክርስቶስ ኢየሱስን ደም በጸሎት መጥራት እንዴት ኃይለኛ እንደሆነ ይነግረናል "እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፤ ይሄውም ዲያብሎስ ነው።" በእንግሊዘኛው የእስትሮንግ መዝገበ ቃላት እንዲሽር የሚለው ቃል "ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ፣ ዋጋ ቢስ ማድረግ አሊያም ማስወገድ" ብሎ ይፈታዋል።

"ሰይጣን ጻድቁን የእግዚአብሔርን ልጅ በሰቀለ ጊዜ ራሱን ነው ያጠፋው። እርሱ የሰው ልጆች ሕግን ጥሷል በማለት የሚያቀርባቸው የክስ ምክንያቶች ሁሉ ከአዳም ውድቀት ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል። መስቀሉ በማንም ላይ ይሁን በምንም ላይ ስይጣን ስልጣን እንዳይኖረው አድርጓል። እርሱ አሁን በማታለልና በማጭበርበር የሚሰራው ሥልጣን ማለት ነው" (ብልሄምየር ፣31)።

የጌታ ኢየሱስ ደም በምንጠራበት ጊዜ ሰይጣንና ጭፍሮቹ ሁሉ የተሸነፉ መሆናቸውን ያስታውሰናል፤ ነፍሳትን ለማዳን በምናደርገው ፍልሚያ ይህ እጅጉን አስፈላጊ ነው። በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም የሰው ልጆችን ዕዳ በሙሉ ከፍሏል (1ኛ ዮሐንስ 2፡2)። ሰይጣን አሁን በእጁ ያሉት ነፍሳት ቀድሞውን በእጁ ስላሉ እንጂ የእርሱ አይደሉም፤ እኛም ቢሆን የጠፉበት እንዲመለሱ ድርሻችንን አልተወጣንም።

ሌላኛው ትልቁ የውጊያ መሣሪያ የኢየሱስ ስም ነው። የጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ለወንጌል ተልዕኮ ከተላኩበት ሲመለሱ ደስ ብሎአቸው "ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንት እንኳ ተገዝተውልናል" (ሉቃስ 10፡17) ብለው ነበር፤ ዛሬም ለእኛ እንዲሁ የተገዙ ናቸው።

በመንፈሳዊው አለም የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለምን ኃይለኛ እንደሆነ የሚያሳዩ ሶስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው እርሱ ፈጣሪ፣ በፍጥረት ሁሉ ላይም ጌታ ነው። "እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናትም ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው" (ቆላስይስ 1፡15-16)። በሁለተኛ ደረጃ እርሱ በመስቀል ሞቱ ጌታ ነው። "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና ደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይሄውም ዲያብሎስ ነው፤ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፤ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" (ዕብራውያን 2፡14-15)። እርሱ ሞትን ድል አድርጎ በመነሳቱ በትንሳኤው ጌታ ነው። "እርሱ መላእክት፤ ሥልጣናትና ኃይላት ከተገዙለት በኃላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡22)። የጠፉ ነፍሳት ነጻ እንዲወጡና ለእነርሱ መማለድ እንዳለብን ጌታ ኢየሱስ ያዘዘውን ትዕዛዝ በቀጥታ ስለምንታዘዝ እነርሱን የያዙ አጋንቶች መታዘዝ አለባቸው፣ ምክንያቱም እነርሱ ለእርሱ ስም ይገዛሉና።

የእግዚአብሔር ቃል በጸሎት የምንጠቀመው ሌላኛው የውጊያ መሳሪያ ነው። ከዚህ በፊትም እንዳየነው ቃሉን መጠቀም ወይም መጥቀስ በጣም ውጤታማ ነው። የእግዚአብሔር ቃል "የመንፈስ ሰይፍ" ተብሏል (ኤፌሶን 6፡17)።

ሰይጣን ኃይሉንና ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ በመስቀል ላይ ስላጣ (ቆላስይስ 2፡15፤ ዕብራውያን 2፡14) እርሱ የሚያደርገው ሁሉ ውሸት ነው። በውሸት "አለሙን ሁሉ ማታለል" (ራዕይ 12፡9) እንዴት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። የእግዚአብሔር ቃል "እውነት" ነው፤ እውነት ሁልጊዜ ውሸትን ያሸንፋል። በመንፈሳዊ ውጊያ ጦርነት በጸሎት ወቅት ቃሉን ሁልጊዜ ብንጠቀም እናሸንፋለን፣ ነፍሳትም ነጻ ይወጣሉ! ምሥጋና ሌላኛው ኃይል የተሞላ የውጊያ መሳሪያ ነው። እግዚአብሔርን ማመስገን ስንጀምር እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሁኔታዎች ይመጣል (መዝሙር 22፡3)፤ በጦርነት ጊዜ "የጦሩን አዛዥ" በቦታው ማግኘት እንዴት የሚያስደስት ነገር ነው! የምስጋና ኃይል የጥሩ ምስክርነት ተምሳሌት እንደሆነ በ2ኛ ዜና 20 ላይ ተገልጿል። ይሁዳ ከተለያዩ አገራት በመጡ ጣምራ ጦር ተከባ ነበር፤ ሁኔታው በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ንጉስ ኢዮሳፍጥ "ይሁዳ ሁሉ ይጸልዩና ይጾሙ" ዘንድ ጠርቶ ነበር።

“ዝማሬውንና ምስጋናውን በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞአብ ልጆች በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦር አመጣባቸው፤ እነርሱም ሞቱ” (ቁ.22)፡፡
ለነፍሳት በምናደርገው ትግል ምስጋና ምን ያህል ኃይል እንዳለው አብዛኛዎቻችን መረዳቱ የለንም፡፡ ምናልባትም ለዚህ ይሆን አስደናቂውን ኃይል ያልተጠቀምነው? ጆን ሐይድ ለነፍሳት በሚያቀርበው ጥያቄ የምስጋናን ትልቅ ሚና ፍራንስስ ማክጎግ እንዴት እንደሚጋራው እንመልከት፡፡ “ጆን ለእኔ ሲነግረኝ አስታውስ ነበር፣ እርሱ እንዳለ በእነዚያ ቀናት በአንዲቱ አራት ነፍሳት ባይመጡ ኖሮ፣ ስሜቱ አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት ይቸገር፣ መብላትና ማንቀላፋት አይችልም ነበር፡፡ የበረከት እንቅፋት ምን እንደሆነ እንዲያሳየው ጌታን ጠየቀ፡፡ በሚያስደንቅም ሁኔታ በሕይወቱ የምስጋና ፍላጎት እንዳለ ተረዳ፡፡ በእግዚአብሔር ቃል በብዙ መቶዎች ጊዜ ተደጋግሞ የተነገረው ይህ ትዕዛዝ (ምስጋና) በርግጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም እርሱ ኃጢአቱን ተናዞ በደሙ ኃይል ይቅርታን ተቀበለ፡፡ እንደ ማንኛውም የእግዚአብሔር ሥጦታ የምስጋናን መንፈስ ለመቀበልም ጠየቀ፡፡ በተገለጠው የክርስቶስ ጸጋ ማንነቱ ሲቀየር፤ ሀዘኑም በክርስቶስ ደስታ ዘይት በክብሩ መንፈስ የምስጋና መጎናጸፊያ (የበጉ መዝሙር፡- እግዚአብሔርን ገና ሊያደርግ ስላለው ነገር አመስግኑት) ሲያመሰግን ነፍሳት ወደ እርሱ እንዲመጡ፣ የጎደሉ ቁጥሮችም እንዲሞሉ ሆነ” (ኬር፣ 39)፡፡
ጾም ሌላኛው ትልቁ መሳሪያ ቢሆንም፣ የተጠቀምነው በጥቂቱ ነው፡፡ በውጊያ መጠቀም ካለብን መሳሪያ ውስጥ “ትልቁ ኃይል ያለው” በጸሎት ነው፤ ጾም የጸሎትን ኃይል ቢያንስ በአሥር እጥፍ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የውጊያችን አላማ ጠላትን ማሸነፍ ነው፤ ጾም ውጊያውን በውጤታማነት እንድናጠናቅቅ ያደርጋል፡፡ ኢሳይያስ 58፡6 “እኔ የምደሰትበት ጾም የጭቆና ሰንሰለትና የፍትሕ መጓደል ቀንበር ታላሉ ዘንድ፣ ቀንበሩን ሰብራችሁ የተጨነቁትን ነጻ ታወጡ ዘንድ አይደለምን?” ይላል፡፡ በአንድ ወቅት ደቀመዛሙርት አጋንንትን ከትንሽ ልጅ ውስጥ ማውጣት ባልቻሉ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ተናገራቸው “እንዲህ ዐይነቱ በጸሎትና [በጾም] ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም አይወጣም” (ማር 9፡29)፡፡

ሌላኛው በመንፈሳዊ ውጊያ ወቅት በስራ ላይ የሚውል የውጊያ መሳሪያ ፍቅር ነው። ጌታውን ከሙሉ ማንነቱ የሚቀበል፣ የጠፉትን ነፍሳት እንደ ራሱ የሚወድ ሰው ማንም ሊያቆመው አይችልም። ራዕይ 12፡11 “እነርሱ በበጉ ደምና በተናገሩት ምስክርነት ቃል ድል ነሥተውታል፤ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል” ይላል።

አንድን ሰው እስከ መጨረሻ የምትወድ ከሆነ ይህ ሰው ወደ ሲኦል እንዳይሄድ የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ ትከፍላለህ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፍቅር መቼም አይወድቅም። “ፍቅር ያለው ሰው ሁሉን ይችላል፤ በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል፤ በሁሉም ላይ ተስፋ ያደርጋል፤ በሁሉ ነገር ይጸናል። ፍቅር ያለው ሰው ምን ጊዜም አይወድቅም፤” (1ኛ ቆሮንቶስ 13፡7-8)

እግዚአብሔር የሰጠንን የውጊያ መሳሪያ ተጠቅመን በምንጸልይበት ጊዜ ምንድነው የሚሆነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4-5 እንዲህ ይላል “የጦር መሣሪያዎቻችን ምሽግ ለማፍረስ የሚያስችሉ ልመለኮታዊ ኃይል እንጂ ዓለማዊ የጦር መሣሪያዎች አይደሉም። እግዚአብሔርን በማወቅ ላይ እንቅፋት ሆነው የሚነሡትን ክርክርና ትዕቢት እናፈርሳለን፤ የሰውን ሐሳብ ሁሉ እንማርካለን፣ ለክርስቶስም እንዲታዘዙ እናደርጋለን።

በጸሎት የምንጠቀማቸው መሳሪያዎች ከፍተኛ ኃይልን ለመቋቋምና ወደታች ስቦ ለመጣል፣ እስተሳሰብን ለመማረክና ትኩረት ለመሳብ ይጠቅማል። የሰው አዕምሮ የእግዚአብሔርን ቃልና ፍቃድ የሚቃወሙ ነገሮችን ይይዛል። አዕምሮ የውጊያው ሜዳ መሆኑን ወዲያው እንረዳለን፤ ጉዳያችን ከአዕምሮ አሰራር፤ አስተሳሰብ እና ሐሳብ ጋር የሚሆነውም ለዚሁ ነው።

ይህንን መረዳት ለእኛ በጣም ጠቃሚ ነው ምክንያቱም እዕምሮን የተቆጣጠረ ሁሉ የሰውን ሁለንተና ይቆጣጠራል። ሰይጣን ያልዳነን ሰው አዕምሮ መቆጣጠር ከቻለ ሰውዬው መዳን እንዳይችል ይቆጣጠራቸዋል ማለት ነው። ይህን ለማድረግ እርሱ የሚጠቀምበት ብቸኛ መንገድ ሰውዬው የወንጌልን እውነት እንዳይረዳ ማሳወር ነው። ማንኛውም ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው በማናቸውም ጊዜ ከሰይጣን ይልቅ ኢየሱስን ከሲኦል ይልቅ መንግሥተ ሰማያትን ይመርጣል። ሌጌዎን ሰይጣን ከያዘው



ጌርጌሶናዊው ሰው ውስጥ ኢጋንንቱ በወጣ ጊዜ ለራሱ ትክክል የሆነውን መምረጥና ማሰብ ችሏል፤ ኢየሱስን በመምረጥም የእርሱ ኃይለኛ ወንጌላዊ ሆኗል (ማርቆስ 5፡15-20)።

“የሰው ልጅ ነጻ ፍጥረት ነው፤ አሮጌውን ማንነት ለመጠቀም ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነ ፍቃድ አለው። ሆኖም በምድር ላይ ከሁሉ የሚበልጥ ባሪያ ሆኖ ተገዛ፤ ለኃጢአትና ራስ ወዳድነትም አልፎ ተሰጠ። የእኛ ጸሎት ግብ ፈቃዱን መግፋት ሳይሆን፣ ተጽዕኖ የሚፈጥረውን አስተሳሰብ የሚያጣምመውን ነጻ ማውጣት ነው። ይህ በእርሱ አይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ በማውጣት እይታውን እንደማስተካከል ይቆጠራል። ሰው አንዴ ነጻ ከሆነና በትክክል ማየት ከቻለ፤ ማንኛውም ነገር ተጽዕኖ ሳያደርግበት የራሱን ፈቃድ የሚመርጥ ሚዛናዊ ይሆናል። የእኛ ጸሎት “ከክፉው እንዲያድነው፤ ኢየሱስ በጠላት ላይ ድልን በመጎናጸፉ የማዳን ሥራው እንዲገለጥ መሆን አለበት። ያለምንም መጠራጠር በእንዲህ አይነት ጸሎት በልባችን ውስጥ ያለውን ደህንነትን ማረጋገጥ እንችላለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚደረግ ጸሎት የጠላት ውጊያ ሜዳ ከሆነው የሰውየው ፈቃድ ነጻ ማውጣት፣ ትክክለኛውንም እንዲመርጥ ያደርጋል” (ጎርዶን፣192-194)።

እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሰይጣንን ኃይል ዝቅ ለማድረግ እንደሚጠቀምበት መረዳት አለብን። ሰይጣን የራሱን ኃይል በሰዎች ሕይወት እንዴት እንደሚያተርፍና እንደሚጠቀም እንመልከት። ከማንኛውም ኃይል ይልቅ የሚበልጠው አለማመን ነው፤ በዳኑና ባልዳኑ ነፍሳት መሓል ያለ ትልቅ



ኀይል ነው። ክርስቲያኑ አማኝ በእግዚአብሔር መንግሥት እንዲጠነክርና ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ነው። ሰይጣን ያልዳነው ሰው በጌታ ኢየሱስ አዳኝነትና አምላክነት እንዳያምን የሚያደረግ ዕቅድ አለው።

አለማመን አንድን ሰው ወደ ሲኦል የሚወስድ ብቸኛ ኃጢአት እስከሆነ ድረስ ሰይጣን ዋጋ እንደሌለው ነገር በመቁጠር

ከሌሎች ነገሮች ጋር በማገናኘት አጠንክሮ ይይዛል። የእግዚአብሔርን ፈቃድና ቃል የሚቃወም ማንኛውም አዕምሮ ይህን ተግባራዊ ያደርጋል። ባለጸጋው መሪ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዴት መግባት እንደሚቻል በጠየቀው ጊዜ፣ ኢየሱስ እንዴት መዳን እንዳለበት በጭራሽ አልተናገረም። ይልቁንም ሐብቱን ለድሆች እንዲያካፍል ነበር የተናገረው። ወጣቱ ባለጸጋ ሰው ግን ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ያለአንዳች ትርፍ በኪሳራ ተመለሰ። ኢየሱስ ስስታምነት የእርሱን ልብና አዕምሮ እንደተቆጣጠረው ያውቅ ነበር፤ ይህም ከመዳን ከለከለው። ይህ በተቃዉሞ እስካልተሰበረ ድረስ ወንጌል ውጤታማ ሊሆን አይችልም (ማርቆስ 10)።

የሰማሪያይቱን ሴት ከማመን የሚከለክላት ትልቁ ነገር የዚህ አለም ምኞት ነበር። ከኢየሱስ ጋር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ብትወያይም፣ ስለ ሕይወት አንዳች አላነሳችም። ኢየሱስ በቀጥታ እርሱዋ አምስት ጊዜ እንዳገባች አሁን ደግሞ ከወንድ ጋር እንደምትኖር በገለጸ ጊዜ ትኩረቷን ሁሉ ሳበ። በዚህም ሁኔታ እርሷን ያሰራት ትልቅ ነገር ተመታ፣ አስደናቂ የሆነውንም መዳን አገኘች (ዮሐንስ4)። ሰይጣን ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍቅር እውነት ለመገደብና ተቀባይነት እንዳይኖር ለማድረግ የሚጠቀመው መራርነትን ነው። ለምሳሌ፡- አንዲት ሴት ልጅ አሁን ጾታዊ ጥቃት ቢደርባት፣ ከጥቂት ጊዜያት በኃላ ደግሞ አንድ ሰው ወንጌልን ቢሰብክላት፣ መልዕክቱ በልቧ ያለውን መራርነት አልፎ አይዘልቅም። የእግዚአብሔር ፍቅር መልካም ዜና መቀበል እንድትችል በውስጧ የሚከለክለው ትልቁ ነገር በጸሎት መነሳት አለበት።

በግብረሰዶም የተያዙ ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ከባድ ነው። እግዚአብሔር ለእነርሱ ፍቅር ስሌለው፣ ወንጌል ኃይል ስላጠረው ወይም ሰዎች ለእነርሱ ስለማይጠነቀቁ አይደለም። ነገር ግን ይህን ለመስበር ትልቅ ጸሎት፤ ጾም፤ ጽናት፤ እምነት የመሳሰሉት ይጠይቃል። ሆኖም ብዙ ጊዜ ድሉን ከማግኘታችን በፊት በብዙ ተስፋ እንቆርጣለን።

አንድ ቀን እኔ ለአንድ ሰው በምጸልይበት ጊዜ ይህ ሰው ለምን ወንጌልን ለመቀበል እንቢ እንደሚል እንዲገልጥልኝ ጌታን ጠየኩት። ጌታም “ቁጥጥር” የሚለውን ቃል በአምሮዬ ውስጥ ሞላኝ፤ ይህን በፍጹም አልተረዳሁም ነበር። ነገር ግን እርሱን ይበልጥ እየተረዳሁ በሄድኩ ቁጥር፣ በራሱ ዙሪያ ያሉ ነገሮች እንደ ብረት አጥር አድርገው እንደተቆጣጠሩት ተረዳሁ። ቁጥጥር

የሚለው ቃል በዚህ ሰው ሕይወት ጌታ እንዳይገባ ምክንያት መሆኑን አወቅሁ። ሰው በጌታ ለመዳን ትሑት መሆን አለበት።

የዚህ መጽሐፍ አላማ በጥልቀት ስለሚያግዱ ነገሮች እንድናጠና ባይፈቅድም፣ በተለያዩ ሱሶች ማለትም በድራግ እና በአልኮል ሱስ ውስጥ ላሉ ሰዎች ለሚጸልዩ ሰዎች በጥቂቱ መናገር እፈልጋለሁ። ይህ ሱስ እውነቱን ከድኖ የያዘ ጭንብል ብቻ ነው። ትልቁ ችግር ሁል ጊዜ በራስ ማንነት ውስጥ ተደብቆ ከሚነሳ የማንነት ጥያቄ ሲሆን፣ መገፋት፣ ጥቃት፣ ወይም ከፍተኛ ሐዘን ሊያካትት ይችላል። ሱስ እነዚህን ችግሮች ሁሉ መደበቂያ ወይም መሸፈኛ ያደርጋል። ስለዚህ ጌታ ድል እንዲሰጠን የችግሩን ዋና ሥር እንዲያመላክተን መጸለይ አለብን።

ኤዲ ሲሚዝ የተባለው ሰው አንድ ምክር ፈላጊ ሴትን እንዴት መርዳት እንዳለበት ሲያስብ እግዚአብሔር እርሷ ያለችበት ሁኔታ እንዲያሳውቀው ይጠይቅ ነበር። እግዚአብሔርም ኤዲን “የአገሪቱ ምዕራባዊ ጭፈራ” ስለተባለው እንዲጠይቃት ነገረው። እርሱም በጠይቃት ጊዜ በመገረም በእንባ ተሞልታ እየጮኸች “ስለዚህ ነገር ማን ነገረህ” አለችው፤ እድሜዋ 15 በሆነ ጊዜ ወደ ምዕራባዊ ዳንስ ቤት አብራ እንደምትሄድ ገለጸችለት። እዚያም የሰንበት ትምህርት ቤት በአንድ ጠርዝ ጨለም ባለ ቦታ ላይ ሆኖ ሲንገዳገድ አየች። ከዚያ በኃላ እዚያው ቦታ ሆና ለእግዚአብሔር ጀርባዋን በመስጠት እንዲህ አለችው “ክርስቲና ማለት በአጠቃላይ ይህ ማለት ከሆነ ለራስህ ውሰደው”። ለኤዲም እንዲህ ስትል ነገረችው “ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕይወቴ ሕያው የሆነ ሲኦል ሆነ፤ እኔም ተስፋ በመቁረጥ የአልኮልና ሕገወጥ ዕጽ ተጠሚ ሆንኩኝ። በተደጋጋሚ የተለያዩ ጋብቻዎችን ፈጽሜአለሁ፤ በአጠቃላይ ግራ የተጋባች ሰው ሆንኩኝ። የእርሱዋን ችግር መሰረታዊ ምክንያት በማወቁ ኤዲ ወደ እግዚአብሔር ጸለየና እግዚአብሔር ከእሥራት ነጻ አወጣት (ስሚዝ ፣71-73)።

ሰይጣን ሰዎች ወደ እምነት እንዳይመጡ የሚያደርጉ ከመቶ በላይ ነገሮችን ይጠቀማል ብዬ አስባለሁ። መረዳት ያለብን መሰረታዊ እውነት ቢኖር በጌታ ካላመነ ከእንዳንዱ ሰው ጀርባ ሰዎች ወንጌልን እንዳይቀበሉና እንዳይድኑ የሚያደረግ ጠንካራ ምክንያት አለው። ምንም እንኳ ግለሰቡ በብዙ ኃጢአት ቢያዝም፣ ውጊያው ከብዙ ኃጢአቶች በአንዱ ላይ ነው። የእርሱ መሳሪያ

በተደመሰሰ ጊዜ ተሸናፊ ይሆንና ሰውዬው ደህንነትን ለማግኘት ይዘጋጃል። (ሉቃስ 11፡21-22)።
ነፍሳትን በማዳን ሂደት ውስጥ በመንፈሳዊ ውጊያ አለም ሌላኛው ጠቃሚ የሆነው ነገር በክርስቶስ ያገኘነውን ስልጣን መጠቀም ነው። እርሱ የራሱን አስደናቂ የሆነ ሥልጣን ሰጥቶናል (ማቴዎስ 16፡19)። "ትራፊክ ፖሊስ በመንገድ ሆኖ በተሰጠው ስልጣን በመንገድ ሆኖ ተሽከርካሪዎችን እንደሚያዝ ሁሉ እንደዚሁ አማኝ በሰይጣን ግዛት ውስጥ ሆኖ በእስራት ላሉ ነፍሳት መጸለይና ነጻ እንዲወጡ ማድረግ ይችላል። በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ኃይል የጨለማ ጉልበት ይሰበራል፤ በክርስቶስ ያለንን ኃይል ስንጠቀም ማንም ሊቋቋመን አይችልም። እግዚአብሔር የእርሱን ኃይል የምንጠቀምበት መሳሪያ አድርጎናል። በእምነት ይህን ሥልጣን ተቀብለን ተቃውሞን ሳንፈራ ጸንተን እንቁም። እርሱ በእኛ ሆኖ ያልጠበቅናቸውን ነገሮች ሁሉ ያከናውናል" (ኤፐፐ፣ 108-110)።
ከሕጋዊነት አንጻር ሁሉም ነፍስ የኢየሱስ ነው፤ እርሱ ለኃጢአተኞች ሁሉ በመስቀል ዋጋ ከፍሏል (1 ዮሐንስ 2፡2)። ሰይጣን ሕገወጥ ኃይል በተሞላ መልኩ በግዞቱ ሰዎች እንዲቆዩ ያደርጋል፤ ሊለቃቸውም ፍቃደኛ አይደለም። እኛ ያለንን ኃይል ሁሉ እስክንጠቀም ድረስ ሰይጣን በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋል። የተሰጠንን ኃይል በክርስቶስ ደም ተጠቅመን በፍጥነት ማስለቀቅ አለብን።
ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም ፍጹም የሆነ ዋጋ ስለከፈለ አንዲትም ነፍስ ወደ ሲኦል እንድትሄድ አይፈልግም። ማንኛውም ነፍስ ወደ ሲኦል እንድትሄድ ምክንያት የሚሆነው ሥልጣናችንን ተጠቅመን፣ ከኃይለኛው እስራት ሰዎችን ነጻ በማውጣት ወደ ደህንነት አለማድረሳችን ነው።
የጦር ጀነራሉ ጆናታን ዌይንራይት ከሌሎች የጦር ወንጀለኞች ጋር በመሆን ፎርሞሳ በምትባል ደሴት ነበር። ውጊያው ቢጠናቀቅም የጃፓኑ አዛዥ ለእነርሱ ምንም መልዕክት አላደረሰም፣ አልፈታቸውም። የጦር አውሮፕላን የድል መልካም ምስራች ዜና ይዛ በመምጣት በደሰቲቱ ላይ አረፈች። በዚህ ጊዜ ጀኔራል ዌይንራት ለጃፓን አዛዡ እንዲህ አለ "የእኔ ጦር አዛዥ ያንተን የጦር አዛዥ አሸንፏል"። እኛም ለኃይለኛው ሰው (በሰው ሕይወት ውስጥ ላለው ለኃይለኛው ሰይጣን) "የእኔ የጦር አዛዥ ያንተን የጦር አዛዥ አሸንፏል"

ማለት አለብን። አግባብነት ከሌለው እሥራት ሰዎችን መፍታት፣ ነጻ ማውጣትና ማዳን አለብን።
በመጨረሻ ነገር ግን በጣም አስፈልጊ የሆነ ነገር ለነፍሳት ስንጸልይ ያለማቋረጥ ዲያብሎስን መቋቋም ነው። የእግዚአብሄርን የጦር መሳሪያዎችን እንድንታጠቅ ታዘናል (ኤፌ 6፡10-18) በዚህም "የጠላትን የውጊያ ስልት እንቃወማለን በክፉ ቀንም መቋቋም እንችላለን። የነፍሳት ደህንነት ጉዳይ ላይ ትኩረት ከሰጠን ሰይጣን እኛ ተስፋ ቆርጠን እንድናቆም እኛ በምንጸልይላቸው ሰዎች ሆነ በእኛ ሕይወት ዙሪያ ከባድ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ለዚህም ነው ሚስት የምትጸልይለት ባል ወይም እናት የምትጽልይለት ወጣት ከመሻሻል ይልቅ እየተበላሸ የሚሄደው። ሰይጣን እነርሱ ጸሎታቸውን እንዲያቆሙ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም እርሱ በእነዚህ ሰዎች ላይ ያለውን ተስፋ እያጣ ስለሆነ።
ስለዚህ ሰይጣንን መቃወም ማለት መጥፎ የሆኑ ሁኔታዎችና ነገሮች አንተ የምታደርገውን የጸሎት ትጋት እንድታቆም እንዳያደረጉ ማለት ነው። አንድ ነገር እሳት የሚከላከል ነው ማለት በእሳት መጎዳትም እንዳለ ያሳያል። እንደዚሁም ውሃ የማይበግረው ነው ማለት ውሃ አይነካውም ማለት አይደለም። ስለዚህ ሰይጣንን መቃወም ማለት እርሱ የሚያደርገው ምንም ይሁን ምንም አንተን ምንም አያደርግም አንተ ለሚድኑ ነፍሳት ጸሎትን ትቀጥላለህ።
ሰይጣንን ለነፍሳት መዳን የመቃወም ትልቅ ምሳሌ የሚሆነው ከዚህ ቀጥሎ ባለው የቻርለስ ብላንቻርድ ምስክርነት ውስጥ ይገኛል። እርሱ የሁኔታን ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ሆኖ ለአርባ ሶስት አመታት አገልግሏል። እርሱም ነገሮች እውነት እንደሆኑ ለማሳየት ከእግዚአብሔር ነገሮችን መቀበል (ጌቲንግ ቲንግስ ፍሮም ጎድ) በሚለው መጽሐፍ ላይ እንዲህ ብሎ ጽፎታል።
ወገኖቼ ከዛሬ ሁለት ተኩል ወይም ሶስት አመት በፊት በፊላዴልፊያ ሆስፒታል ውስጥ ነበርኩ። እኔም በፔልሴልቪንያ መንገዶች ኢንጂነር ነበርኩ የምትጸልይልኝ ሚስት ብትኖረኝም እንኳ እኔ ዘመኔን ሙሉ ኃጢአተኛ ሆኜ ነበር። በዚህ ጊዜ እኔ በጣም ታመምኩና እንደ ምናምንቴ ነገር ሆንኩኝ፤ ዋጋዬም ከአንድ መቶ ፓውንዶች በታች እንደሆነ ተሰማኝ።

በመጨረሻም እኔን ሲከታተለኝ የነበረው ዶክተር ለባለበቴ እርሱ ሞቷል ብሎ ነገራት፤ ይሁን እንጂ እንዲህ አለች “አይደለም እርሱ አልሞተም፤ ሊሞትም አይችልም። እኔ ለእርሱ ሃያ ሰባት አመታትን ሙሉ ጸልያለሁ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ እርሱ እንደምድን ተስፋ ሰጥቶኛል። ስለዚህ እኔ ለሃያ ሰባት አመታት ከጸለይኩና እግዚአብሔርም ተስፋ ከሰጠኝ በኃላ ሳይድን ይሞታል ብለህ ታስባለህ? ዶክተሩም ጥሩ “እኔ አንች ስለሚትይው ነገር ብዙም አላውቅም ነገር ግን እርሱ እንደሞተ ነው የማውቀው” አለ። ከዚያም በኃላ በሕይወት ያለውን ከሞተው የሚለየውን መጋረጃ ዶክተሩ ዘረጋው።

ባለቤቴም ማመን እንድትችል ሌሎች ሰባት ሐኪሞች በየተራ እየመጡ መሞቱን የሚያረጋግጡ ነገሮችን በመግለጽ ቀድሞ የተናገረው ሐኪም ያለውን ሐሳብ እየደገሙ ተናገሩ። ስለዚህ ሰባቱም ዶክተር እኔ እንደሞትኩ ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ግን ባለቤቴ በመኝታዬ አጠገብ ተንበርክካ እኔ እንዳልሞትኩ እያሰላሰለች ነበር። የምታሰላስለውም እኔ የሞትኩ ብሆን እንኳ እርሱ ወደ ሕይወት እንደሚመልሰኝ ምክንያቱም እርሱ ለእርሷ እኔ ሳልሞት እንደምድን ተስፋ ገብቶላት ነበር ብላ ነው። እርሷም ተንበርክካ የነበረችው በእስቸጋሪው የሆስፒታሉ ወለል ላይ ስለነበር ደከማት ጉልበቷ አካባቢም የሕመም ስሜት መሰማት ጀመረ። እርሱዋም ነርሷን ትራስ እንድትሰጣት ጠይቃ ትራሱ ከመጣ በኃላ ተቀብላ ተንበረከከችበት።

አንድ ሰዓት ሁለት ሰዓት ሶስት ሰዓት አለፈ። የመሸፈኛ መጋረጃውም ከአልጋው አጠገብ አሁንም አለ። እኔም እዚያው አልጋው ላይ እንደሞትኩ ሆኜ ተኝቻለሁ። አምስት፤ ስድስት፤ ሰባት፤ እያለ አስራ ሶስት ሰአታት አለፉ፤ ይህም የሆነው ሚስቴ በአልጋው አጠገብ ተንበርክካ እያለች ነው። በዚህ ጊዜ እርሷ እንድትሄድ ሰዎች በነገሩአት ጊዜ እንዲህ ብላለች “አይሆንም እርሱ መዳን አለበት። እርሱ ሞቶ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ያስነሳዋል። እርሱ አልሞተም፤ እርሱ እስካልዳነ ድረስ መሞት አይችልም።

ከአስራ ሶስት ሰዓታት በኃላ እኔ አይኔን ከፈትኩኝ እርሷም እንዲህ አለች “የእኔ ውድ ምን ትፈልጋለህ? እኔም “ወደ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ” አልኩኝ። እርሷም “ወደ ቤት መሄድ አለብህ” አለች። በዚህም ጊዜ ያደረገችውን ሁሉ በማየት ዶክተሮች እጃቸውን በድንጋጤ በማንሳት “ለምን? መሄዱ ይገድለዋል፤ ይህም ደግሞ ነፍስ ማጥፋት ነው” አሉ። እርሷ ግን “እናንተ

የእናንተን ተራ ጨርሳችኃል፤ እናንተ እርሱ ሞቷል በቃ ብላችኂል፤ ስለዚህ እኔ ወደ ቤት እወስደዋለሁ” አለች።

አሁን እኔ 246 ፓውንድ ክብደት አለኝ። አሁንም በፔንስቨላ መንገዶች ላይ በፍጥነት አየሮጥኩኝ ልምምድ አደርጋለሁ። እኔ ለአጭር ጊዜ ሚኒስ ፖሊስ በሚባል አካባቢ ትንሽ ለዕረፍት በሄድኩበት ኢየሱስ ሊያደርግ የሚችለውን እየነገርኩኝ ነበርኩ። ዛሬም ደግሞ ለአንተም ኢየሱስ ምን እንደሚያደርግ ለመናገር ደስተኛ ነኝ። (ብላንቻርድ 94-95)

ለነፍሳት መዳን የሚደረግ ጸሎት የማይመለስበት ሁለት ምክንያቶች ብቻ አሉ። ይሄውም የሚጸልየው ሰው በኃጢአት ውስጥ አለ ወይም አያምንም አለበለዚያ ሰይጣን መልሶ እንዳይመጣ ይከላከላል። ስለዚህ ሕይወትህ በአግዚአብሔር ፊት ትክክል ከሆነ (ዮሐ 15፡7)፤ በጸሎትም የምትቀጥል ከሆነ መልሱ ይመጣል፤ ሰይጣንም ብርቱ ሆኖ መቀጠል አይችልም፤ ስለዚህ የውጊያ ጸሎትህን ሞቅ አድርግ።

በውጊያ ጊዜ ዕቅድ ማድረግ ግድ ነው። ወታደሮች ዝም ብለው ወደ ተለያዩ ነገሮች እየተኮሱ ወደ ፈለጉበት ሁሉ አይሄዱም። ለነፍሳት በሚደረገው መንፈሳዊ ውጊያም ነገሩ እንደዚህ ነው ስልት ያስፈልገናል። እስቲ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ልስጣችሁ።

ለሁሉም ቤተክርስቲያናት የመጨረሻው ስልት ራሳቸውን ለጸሎት መስጠት ነው። ይሄንኑ የጥንት ቤተክርስቲያን አድርጋለች “እነዚህ ሁሉ በአንድ ልብ ሆነው በጸሎት ይተጉ ነበር” (የሐዋ 1፡14) በሚያስደንቅ ሁኔታ ውጤቱ - “በዚያም ቀን ሶስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመረ” (የሐዋ 2፡41) ደግሞም “ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፤ የወንዶችም ቅጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ” (የሐዋሪያት ሥራ 4፡4)

በሌላ የጸሎት ስብሰባ “ከጸለዩም በኂላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ” (ሐዋሪያት ሥራ 4፡31) በተጨማሪም ነፍሳት ሲጨመሩ “ብዙሃን ወንዶችና ሴቶች” (የሐዋሪያት ሥራ 5፡14)፤ “የሐዋርያትም ቁጥር በኢየሩሳሌም በዛ” (የሐዋሪያት ሥራ 6፡7)፤ “በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ዘወር አሉ” (የሐዋሪያት ሥራ 9፡35)። እናም ለሌሎች ብዙ ክፍሎች በዚህ በሐዋርያት መጽሐፍ እንዲህ አይነት ድርጊትን የሚገልጹ

አሉ። የዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ይህንን የጥንት ቤተክርስቲያን የጸሎት ፈለግ ብትከተል ተመሳሳይ የሆነ የወንጌል እንቅስቃሴ ውጤት ይከሰታል።
ሌላኛው ጥሩ ውጤታማ የሆነ ስልት የጸሎት ቡድን ማቋቋም ነው። ለዚህም ጥሩ የሚሆነው በብዙ ቤተክርስቲያናት ያለው በየጊዜው የሚካሄዱ የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም የቤት ኅብረቶች ናቸው። አነርሱም ሳይቋርጡ ተግተው ለጠፉ ነፍሳት ወደ ክርስቶስ እስኪመጡ ድረስ መጸለይ ይችላሉ።
ኤቬኒሊ ክርስተንሰን ሶስትዮሽ ጸሎት ውጤታማ ነገር ግን የወንጌል ሥርጭት ከመደረጉ በፊት ቀድሞ ከሚደረጉ ጸሎቶች ሁሉ ቀላል እንደሆነ ተናግራለች። ይሄም ምንድነው ሶስት ክርስቲያኖች በፍቃደኝነት በየሳምንቱ ለዘጠኝ ላልዳኑ ነፍሳት የሚጸልዩት ጸሎት ነው። እርሱዋ እንደምትገልጸው እንዲህ አይነት ውጤታማ ጸሎት የታየው ብልግርሃም በእንግሊዝ ባደረጉት ሁለት ክሩሰዶች ላይ በታየው ውጤት ነው። “የሶስትዮሽ ጸሎት ብልግርሃም በ1984 በእንግሊዝ እስካደረጉት ክሩሴድ ድረስ ጥሩ ውጤት ያሳየ ነው። ዘጠና ሺህ የሚያህሉ ሰዎች በሶስትዮሽ ጸሎት በመጣመር ኩሩሴዱ ከመደረጉ በፊት ይጸልዩ ነበር። እያንዳንዱ ሶስት ክርስቲያኖች እያንዳንዳቸው ጌታን የማውቁ ሶስት ሰዎች ይመርጡ ነበር። ከዚያም የቀጣይ አመት ኮንፍራንስ ከመደረጉ በፊት አመቱን ሙሉ በየሳምንቱ እየተገናኙ ለነዛ ዘጠኝ ሰዎች ጌታን እንዲያውቁ ይጸልያሉ። በጥር 1989 የውሳኔ መጽሔት ለብልግርሃም ሁለተኛ ዙር የወንጌል ኪሩሴድ ለሚደረገው ኮንፍራንስ የሶስቲዮሽ ጸሎትን በማበረታታት አብዛኛዎቹ በዚህ ሶስትዮሽ ጸሎት የታቀፉ ሰዎች ዘጠኙ ሰዎቻቸው ብልግርሃም ወደ እዚያ ከመምጣቱ በፊት ጌታን መቀበላቸውን ተመልክተው ነበር። ወደ ሰባት ሺህ የሚደርሱ ሰዎች ብዙሃንን ባቀፈው ለብልግራም ኪሩሴድ በተደረገ የሶስትዮሽ ጸሎት በውጤቱ ምድር ግርምትን ሞላች። ይህ እንዴት ያለ ነፍሳትን ለማዳን በአለም ሁሉ አስገራሚ ከሰይጣን ጋር የሚደረግ መንገድ ነው!” (ክርስተንሰን፣ 110)።
ነፍሳት እንዲድኑ በምናደርገው ጸሎት ውስጥ የጸሎት ጓደኛ ወይም ጥምረት ለሌላኛው ውጤታማ መንገድ ነው። ብዙ ሆኖ ከመሰብሰብ ሁለት ሆኖ መሰብሰብ በጣም ቀላል ነው። የባልና የሚስት የጋራ ቡድን በጣም የተሻለ ነው ምክንያቱ እነርሱ ሁል ጊዜ አንድ ላይ ይሆናሉ ደግሞም ለዘመድ ወገናቸው ያላቸው ሸክም ከፍ ያለ ነው። ይሁን እንጂ ማንኛውም የጸሎት

ቡድን ጥምር ይሰራል። ኢየሱስም የጸሎታቸው መልስ እንደሚመጣ አረጋግጧል (ማቴ 18፡19)።

በመጨረሻም በአንድ ሰው ለሚደረግ የግል ጸሎት የሚሰራ አንድ ስልት እጠቅሳለሁ። ይኸውም የጸሎት ዝርዝር ነው። እኔና በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወጌኖቼ አንድ ላይ በመሆን የጸሎት ዝርዝር ዘዴን ለብዙ አመታት ተጠቅመናል፤ በዚህም ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ተመልክተናል። እኔን የባረከኝን ታሪክ በመናገር ላገባድድ፤ ታሪኩ እርስዎንም ይባርካል ብዬ አምናለሁ።

"ከተወሰኑ አመታት በፊት በስፕሪንግ ፊልድ ኢሊዮንስ አንድ ትጉህ ሰው ለራሱ የጸሎት ቡድን አቋቁሞ እንዲህ የሚል ሐሳብ ሰጣቸው፡- "በዚህ ምሽት ወደ ቤት በምትደርሱበት ጊዜ በዚህ በስፕሪንግ ፍልድ ከተማ ያሉ እናንተ የምታውቁአቸው እንዲድኑ የምትፈልጉትን ሰው ስም ሁሉ ጻፉ፤ ከዚያም በስማቸው ሶስት ጊዜ በቀን ጸልዩ ሊድኑ ይችላሉና። በቻላችሁት ሁሉ ጌታን እንዲቀበሉ አግዙአቸውም:"

በዚህ ጊዜ በዚያ ከተማ ውስጥ አካላቶቹዋ እጅጉን የተጎዳ ዋጋ የሌላት ሴት ነበረች። ለአስራ ሰባት አመታት ሁሉ የአልጋ ቁራኛ ሆና ነበር። ለብዙ አመታት ዘርዝር ሳታደርግ በጅምላ ነፍሳት እንዲድኑ ትጸልይ ነበር። የእርሱዋ ቤተሰብ ለዚያ ለጸሎት ቡድን የተሰጠው ሐሳብ በነገሩአት ጊዜ እንዲህ አለች "እኔ ማድረግ የምችለው አንድ ነገር አለ፤ የቀኝ እጁዋን ማንቀሳቀስ ትችላለች። በአልጋዋ አጠገብ ጠረጴዛ ነበረ፤ እስክርቢቶና ወረቀት እንዲሰጡአት ጠየቀች፤ እርሱዋም የአምሳ ሰባት ሰዎችን ስም ጻፈች። ለእነዚህ ሁሉ ስማቸውን እየጠቀሰች በየቀኑ ሶስት ጊዜ ትጸልይ ነበር። ለእነርሱ ያላትንም አክብሮትና መውደድ በመጥቀስ ደብዳቤ ጻፈች። እነዚህን ሰዎች ለሚያውቁ ክርስቲያን ጓደኞች ስለ እነርሱ ሚስጥርን ሁሉ ሊጠብቁ ስለሚችሉ፣ ስለ ደህንነታቸው ስለሚያስቡ በሚችሉት ሁሉ ወደ ደህንነትና ንስሓ እንዲመጡ እንዲረዱአቸው ደብዳቤ ጻፈች። በእግዚአብሔር ያለጥርጥር እምነት ነበራት። በእርሱም ላይ ባላት ሙሉ እምነትና የዋህነት ላልዳኑት ማለደች። ሁሉም ሃምሳ ሰባቱ ሰዎች በአዳኛቸው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ" (ማክኪሉር ፣124-25)።

# ምዕራፍ 6
# የግል ሕይወት ምስክርነት

ይህ ትምህርት በፋርሚርቪል ሉውዚያና በሚገኘው በክሪስትቪው ባፕቲስት ቤተክርስቲያን፣ ግንቦት ወር 2002 አስተምሬው ነበር። የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ዋይኔ ዋይትሳይድ እንዲህ ጽፏል፡- "ከሰዎች ሕይወት ጠንካራ የሚባሉ ነገሮች ተወግደው ሲወጡ አይተናል፤ አንተ ያስተማርከው ይህ ትምህርት የእግዚአብሔርን መርሆዎች በተግባር በማዋል ለጠፉ ነፍሳት ለሚጸልዩ ሰዎች ሕይወት ትልቅ አብዮት እየፈጠረ ይገኛል።"

መጋቢው ዋይኔ በሞት ጎዳና ላይና በእስር ቤት ላሉ ትልቅ ሸክም ያለው ስለሆነ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው እነርሱን ለክርስቶስ በመማረክ በሚያደርገው ትግል ነው። ታሪኩም እንዲህ ሲል ይቀጥላል፡- "በሞት መንደር ያሉትን ማዳን በቴክሳስ ሃውስትቨይል ያሉትን እስረኞች ነጻ የማውጣትን አብይ ሥራ ያካትታል። ይህ ሰው በጣም ራሱን ለእስልምና የሰጠ ሰው ሲሆን፣ በባሕርይው እኔ ከማውቃቸው ከብዙ ክርስቲያኖች የተሻለ ነበር። እኔም ከእርሱ ጋር ለሁለት አመታት አብሬ ሰርቻለው፤ ምንም እንኳ ወንጌልን ለእርሱ በመመስከር ጌታን እንዲቀበል ብረዳውም አንዳች ለውጥ አልታየም ነበር። ደብዳቤ ለእኔ ሲጽፍ "አላህ ከአንተ ጋር ይሁን" በማለት ነበር የሚዘጋው፤ በዚህም በብዙ ተስፋ ቆርጬ ነበር።

በመስከረም ወር 2002 ከእስር ከመፈታቱ ከ2 ወራት ቀደም ብሎ ለቤተክርስቲያን ያሰረውን ትልቁ የስህተት ትምህርት እንዲታሰር፣ የክርስቶስ ደም በእርሱ ላይ እንዲረጭ አጥብቀው እንዲጸልዩ ነገርኳቸው። በሚገርምም ሁኔታ ነገሮች መለወጥ ጀመሩ፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሩ አስተማሪ እንደነበር በማመን፣ ደብዳቤዎችን "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን" በማለት መጻፍ ጀመረ።

ከእስር በሚፈታበት ጊዜ አብሬው እንድገኝ ጋብዞኝ ነበር። ከመፈታቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ወደ ሁንትስቬይል ሄጄ ነበር፤ እርሱም፡- "ለደህንነት በክርስቶስ እንዳምን ምን ማድረግ አለብኝ?" ብሎ በጠየቀኝ ጊዜ ልቤ እንዴት ሐሴት እንዳደረገ መግለጽ አልችልም። ከሰዓታት በኋላም በ9፡05 ጌታ ኢየሱስ የእርሱ አዳኝ እንዲሆን ጠየቀ። በሚገርም ሁኔታ ከአምሳ አንድ ሰዓታትና ከአስራ ሁለት ደቂቃ በኃላ ነፍሱ አረፈች። ከእስር ከመፈታቱ ከሁለት ሰዓታት

በፊት እጁን ወደ እኔ በማንሳት “እወድሃለሁ እኔም በሰማይ እጠብቃሃለሁ” ብሎ ተናገረኝ። እርሱም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በዚህች ምድር ሳለ የተናገረው ቃል “እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ ደግሞም ታላቅ ነው!” ሲሞት ፊቱ በደስታ የተሞላ ነበር፤ ይጠባበቀው የነበረውም ይህንኑን ምስክርነት ነበር።

በሞት ጎዳና ያለውን ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በራሳችን የምናደርገው ማናቸውም ጥረት የስህተት አስተማሪ የሆነውን ኃይለኛውን በማሰር በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ካልሸፈነው በስተቀር ከንቱ ነው። ከዚያ በኃላ አስገራሚ የሆነ የወንጌል በር በቅጽበት ሲከፈት፣ እርሱ ራሱ እንዴት ሊድን እችላለሁ ብሎ ሲጠይቅ ተመለከትን። ዛሬ እርሱ በሰማይ አለ፤ ይህም የሚሆነው እኛ ለጠፉት ሰዎች በተለይም ኢየሱስ በማቴዎስ 3፡27 ላይ እንዳለው ኃይለኛውን በማሰር ለሚጠፉት መጸለይን ስንማር ነው። “ለጉባኤያችን ነጻ የማውጣትን እውነት ስለተናገርክ በጣም አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር አምላክ በመጨረሻው ዘመን ታላቅ መከር የመሰብሰብ ስኬት በመስጠት እንዲያጸናህ እለምናለሁ።”

ለአንድ ሰው ደህንነት በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ሰው ዙሪያ ስራውን ይጀምራል። ይህ ነበር ለሪክ ግሬሻ የእርሱ ሚስት ሄሌንና መጋቢዋ ሚኪ ሃንዲኤል በጋራ ሲጸልዩ የሆነው። የሪክ ታሪክ ክፍል እንደሚከተለው ነው፡- “በሕይወቴ ካሳለፍኳቸው በጣም አስጨናቂና አስቸጋሪ ቀናትና ሌሊቶች መካከል አንዱ በ1990፣ በየካቲትና መጋቢት ወር ውስጥ ነው። ምንም እንኳ በጊዜው አንዳች ባልረዳም፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ነበርኩ። ለእኔ እየሆነ ያለው ምን እንደሆነ ባልረዳም እንኳ ይገባኝ የነበረው በእነዚህ ሁለት ወራት በሄድኩባቸው ቦታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድምጽ እሰማ ምስልንም አይ ነበር። ሁልጊዜ እኔ በምነቃበት ሰዓት እግዚአብሔር በዚያ ነበረ። ለብዙ አመታት ሳውቃቸው የነበሩ ሰዎች ስለጌታ ለእኔ መናገር ጀመሩ። የትም መደበቅ አልቻልኩም ነበር።

አንድ ቀን ከጓደኛዬ ጋር ሆነን በእርሱ መኪና ስንነዳ ሳለ ጓደኛው መንገድ ዳር አስቁሞን ያናገርንበትን አልረሳውም። ይህ ሰው በእኔ በኩል ወደ መኪናው ተጠግቶ መናገር ይጀምራል፤ በንግግሩም ለጓደኛዬ ስለ ጌታ ኢየሱስ በመናገር ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ እንዲቀበል ያበረታታው ነበር።

አሁንም ሌላ ድምጽ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማሁ፤ መደበቅ የማልችልበት አይነት ስሜትም ተሰማኝ። በመኪናው ውስጥ ምንም ሳላወራ ቁጭ ብዬ ነበር። በአንድ በኩል ብዙ መስማት ፈለኩኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጓደኛዬ መንዳቱን እንዲቀጥል ፈልጊአለሁ። በመጨረሻ ለአንድ ሰአትና አምስት ደቂቃ ያህል ከቆየሁ በኃላ ጓደኛዬ መንዳቱን ቀጠለ።

ቀናቶች እያለፉ ሲሄድ እግዚአብሔር ራሱን በስፍራ ሁሉ ይገልጥ ነበር፤ በዚያን ጊዜ የራሴን ስራ በማሽን ቤት ውስጥ እሰራ ነበር። አንድ ጥቁር አስተዋይ ሰዉ በየጊዜው ወደ እኔ መጥቶ ከእኔ ጋር ያወራ ጀመር። በዚህ ጊዜ እኔ ነገሮችን እያመንኩ በምመጣበት ሁኔታ እርሱ ወደ ሥራ ቦታዬ አንድ ቀን መጣ። እኔም በራሴ በትዕቢት ተሞልቼ ስለ ጌታ ማንም ሊነግረኝ አይገባም፣ ሁሉን እኔ አውቃለሁ ባይ ነበርኩ፤ ሆኖም በመጨሻ ስለ ጌታ ኢየሱስ መጠየቅ የምችልበት አቅም አገኘሁ። ምንም እንኳ ለእርሱ መልሶች እኔ የተዘጋጀሁ ባልሆንም፣ እርሱ ግን የተዘጋጀ ነበር።

እርሱም “ጥቂት ታገሰኝ ብሎ ወደ መኪናው በመሄድ ለመቶ አመታት ያህል የቆየ የሚመስል መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ መጣ፤ የመጽሐፉንም ገጾች በመክፈት ማንበብ ጀመረ። ያካፍለኝ የነበረውን ነገር ባልረዳ እንኳ ዛሬ በውስጤ የማይረሳ ነገር አለ የሚል ስሜት ተሰማኝ፤ ይህን መቼም አልረሳውም። “ዳግመኛ መወለድ አለብህ” የሚለውን ሐሳብ በተደጋጋሚ ነገረኝ፤ ይህ ከአዕምሮዬ ከቶውን ሊጠፋ አልቻለም።

በዚህ ወቅት እኔን ወደ እግዚአብሔር ቃል ያቀረበኝ ነበር። በውስጤ ካለው ጠንካራ ስሜት የተነሳ አንድን ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ለመጠየቅ ድፍረት አገኘሁ። እኔም በኢንሳይኮሎፒዲያ ክርስቶስ የሚለው ቃል ፈልጌ ሳገኝ፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ያለበት ስዕል አገኘሁ። የጌታ ኢየሱስ ስዕል ላይ ትኩረቴን እንዳደርግ የሆነ ነገር ገፋፋኝ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በየምሽቱ በዚህ ስዕል ሐሳብ መመሰጥ ጀመርኩኝ። በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታትም ሕይወቴ ተቀየረ፤ በብዛት የእርግማን ቃላትን እጠቀም ስለነበር፣ ይህን ማቆም ወደ ማልችልበት ደረጃ ደረስኩኝ። በምችለው አቅም ሁሉ ለመተው ሞከርኩኝ፣ ነገሩ እኔን ተቆጣጥሮት ነበርና እርሱን መቆጣጠር አቃተኝ።

በመጨረሻ አንድ ቀን በሥራ ቦታ ብቻዬን ባለሁበት ለእግዚአብሔር እንዲህ ስል ተናገርኩኝ፡- “ጌታ ሆይ እኔ ይህን መተው አልቻልኩምና እባክህን

እርዳኝ፤ በመስቀል ላይ ያደረከውን ነገር ሙሉ በሙሉ መረዳት አልችልምና አሳየኝ፣ እኔም እከተልሃለሁ። “ከዚያ ቀን ጀምሮ በእኔ ውስጥ የሆነ ነገር ተለወጠ። መርገምን ብቻ አይደለም ያቆምኩት ለመርገም ያለኝን ፍላጎት እንኳ አጣሁት፤ ለመናነገር የሚሆን ቋንቋ እስከማላገኝ ድረስ!

እኔም ለሌላ ሰው በውስጤ ምን እየሆነ እንዳለ ለሌላ ሰው መንገር ነበረብኝ፤ በዚህም መጋቢዎችን ለቤተክርስቲያን የሆነ ነገር ማለት እንደምችል ጠየኩኝ። እኔም ማለት የምችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እኔን በክርስቶስን መውደድ ስለተቀበለኝ፣ ቀሪ ዘመኔ እርሱን መከተል እንዳለበኝ አቅም የሆነኝ እርሱ ብቻ እንደሆነ ነው። በእነዚህ ሁለት የማመን ወራት ያልተረዳሁት ነገር ቢኖር፣ ባለቤትና የእርሷ መጋቢ ለእኔ ደህንነት በየቀኑ ራሳቸውን በመስጠት ሳያቋርጡ ይጸልዩ ነበር፤ ስለማመድም የነበርኩት እግዚአብሔር የእነርሱን ጸሎት ሲመልስ የነበረውን ነው። እኔ የታማኝ ጸሎት ውጤት ነኝ፤ እናንተም በዚህ ጎዳና አልፋችሁ ከሆነ የምለው ምን እንደሆነ ትረዱታላችሁ። በአሁኑ ሰአት የቤተክርስቲያን መጋቢ ነኝ፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ በሕይወቴ ደጋግሜ እየተለማመድኩትም ነው።

እግዚአብሔር ወደ አንድ ሰው በምንጸልይበት ጊዜ ሰውየውን ወደ እርሱ ለማምጣት የሚፈልገውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስድ መፍቀድ አለብን። ዌሲሊ ዱዌል እንዲህ ይላል፡- “ብዙ የጸሎት መልሶች እንዲመለሱ የሚጸልዩ ሰዎች ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ማስገዛት ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔር ዝም ብሎ ሰዎችን ከቦታ ወደ ቦታ ልክ በሰሌዳ ላይ እንዳለ ጽሑፍ የሚያዛዋውር አይደለም፤ ብዙ ግፊትና ተጽእኖ ሰዎች ላይ በማምጣት እንዲፈልጉት ያደርጋል (ዱዌል፣ 262)። ግፊቱ በጣም አስጨናቂ ሊሆን ይችላል። ለቶኒ ፎንቴኖት የሆነው ነገር ይህ ነበር “እኔ የተወለድኩት ትልቅ የጸሎት ጀግኖች ባሉበት ክርስቲያን ቤተሰብ ነው (እናቴ፣ አያቶቼ፣ አክስቶቼና አጎቶቼን ያካትታል)። እነርሱ ለእኔ ምንም እንኳ ለብዙ አመታት ያህል ቢጸልዩም፣ የራሴን ነገር ማድረግ ቀጥዬበት ነበር። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ጉዳይ ሲኖረው የራሳችንን ነገር በማድረግ ቀጥለንበት ሳለ፣ በጣም አስገራሚ ነገሮች እንዲሆኑ መፍቀድ ይጀምራል። ከዚያ በኃላ እርግጠኛ ሆኜ ልንገራችሁ እርሱ በእኛ ሕይወት ትኩረትን ያገኛል።

እግዚአብሔር በሚያዝያ 22 1982 የእኔን ትኩረት ሳበ። እኔም በባቄላ እርሻ ማሳ ውስጥ ኬሚካሎችን መርጨት ጨርሼ ወደ ኃላ ስመለስ አውሮፕላኔ እየበረረ እያለ አደጋ ደርሶት ተቃጠለ፤ በእሳት ውስጥ ነበርኩኝ። እሳቱን ለማጥፋት በመሬት በመንከባለል ሽሚዜ ሙሉ በሙሉ እንደተቃጠለ አየሁ፣ በእጆቼ ላይ ያለው ቆዳ ልክ እንደ ሽረሪት ድር በእጆቼ ጣቶች ላይ ተንጠለጠሉ። ቀኝ አይኔ ማየት አይችልም፣ ሰውነቴ የተለያዩ ፈሳሾችን ማፍሰስ ጀመረ፣ እኔም አደጋ ላይ እንደሆንኩኝ ተረዳሁ።

እርዳታ ለማግኘት መጮህ ጀምርኩኝ፣ ማንም የሚሰማኝ ግን አልነበረም። እኔም መሄድ እስከሚሳነኝ ደረስ የቻልኩትን ያህል ሮጥኩኝ። በዛፍ ስር ተኛሁኝና መጸለይ ጀመርኩ፤ እንዳልሞትኩ የሆነ ሰው መጥቶ እንዲረዳኝ እንዲያደርግ እግዚአብሔርን ለመንኩት። ወዲያውም ነገሮች መቀየር ጀመሩ፤ አንድ ሰው መጥቶ እንደረዳኝና እንዳገዘኝ ያህል በጉልበቴ ብርታት ተሰማኝ። በአዲስ ጉልበት በመሮጥ ወደ አንዲት ፒኪአፕ መኪና ደረስኩኝ፤ ወደ መኪናዋ ቀርቤ እንዲረዱኝም ጠየኩኝ። በሥራ ላይ የነበረ ሰው ወደ እኔ ተመለከተና ሮጦ በመምጣት ወደ ሆስፒታል ይዞኝ ሄደ። ከዚያም ከመጀመሪያው ሆስፒታል ወደ ሌላ በቴክሳስ ጋልቭስቶን ወደ ሚገኝ ጆን ሲሊ ቦርን (መቃጠል) ማዕከል ተወስጄ ሁለት ወራትን በልዩ ትኩረትና ክትትል ቆየሁኝ።

በዚህ በጣም ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር የእኔን ትኩረት ሳበ። በህዳር 1982 ወንድም ሊ ቶማስ በኢንዲያን ቪሌጅ ቤተክርስቲያን ስብሰባ ላይ ትልቅ የመነቃቃት ቃል ሰበከ። ወንጌል ከተነጋረኝም በኃላ ጌታ ኢየሱስ አዳኜ እንደሚሆን አመንኩኝ። እርሱም "ቶኒ ይህ የአውሮፕላን መውደቅና መቃጠል በሕይወትህ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ የሚበልጥ ነገር ይሆናል፤ በዚህ አማካኝነት አንተ ጌታን ወደ ማወቅ መጥተሃልና" አለኝ ። እኔም በሐሳቡ ተስማማሁ።

ኦስዋልድ ቻምበርስ እንዲህ ያላል፡- "እኛ ለሌሎች በምንጸልይበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ማናችንም በማናውቅበት ሁኔታ ማንነታችን ተቆጣጥሮ ይሰራል፤ እኛ የምንጸልይለት ሰው ምን እንደሆነ አይረዳም፤ ነገር ግን ጊዜው ካለፈ በኃላ የጸለይንለት ሰው በመረበሽና ዕረፍት በማጣት ምልክት መስጠት ይጀምራል። የዚህ አይነት የምልጃ ጸሎት ነው ለሰይጣን መንግሥት

አደገኛ የሚሆነው፡፡ ከጅምር ሲታይ ነገሮች በጣም ቀላል የማይሆኑ ይመስላሉ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ምክንያት ሆኖ ባይጨመር ለመታዘዝ እንኳ ፈቃደኞች አንሆንም ነበር” (ቻምበር፣ 102-03)፡፡ ለያዕቆብ ዊሊያምስ የሆነው ነገር ይሄው ነበር፡፡ እርሱ ለረጅም ጊዜ በማመንና መረዳት ውስጥ ቢቆይም፣ የእርሱ ቤተሰቦችና ጓደኞቹ ስለ እርሱ ሸክም ተሰምቶአቸው ሲጸልዩ ነበር ነገሮች ተቀይረው ወደ ደህንነት የመጣው፡፡ በእርሱ ታሪክ ውስጥ “ወደ ዌስትውድ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን በተዛወርን ጊዜ ገና ታዳጊ ወጣት ነበርኩኝ፡፡

እኔም ወዲያውኑ በእምነት ውስጥ ተያዝኩኝ፡፡ ሆኖም ሁልጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን በምሄድበት ጊዜ በውስጤ ከዚህ ሐሳብ ጋር ትልቅ ጦርነት አደርግ ነበር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኃላ ይህ ስሜት ሙሉ በሙሉ ጠፋና ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ፍላጎት ሁሉ ጠፋ፡፡ እናቴም ወደ ቤተክርስቲያን እንድሄድ በጣም ትገፋፋኝ ነበር፤ በተቻለኝ አቅም ሁሉ ከቤት ርቄ ለመኖር እሞክር ነበር፡፡ ይባስ ብዬ እኔ ከአንዲት ሴት ልጅ ጋር መጥፎ የሆነ ግንኙነት ጀመርኩኝ፣ ነገሮችም እየባሱ ሄዱ፡፡

በዚህ ጊዜ ቤተሰቦቼ ስለ እኔ በጣም የከበደ ሸክም ተሰማቸው፡፡ በጌታ ልደት ወቅት ስለ እኔ ለየት ያለ ትኩረት በመስጠት መጸለይ ጀመሩ፡፡ ከቤተሰብ ጋር ያለኝን ቅርርብ ለማጥፋት ከመፈለግ የተነሳ አምሽቼ ነበር የምመጣው፡፡ አባቴ በሌሊት ተነስቶ ስለ እኔ መንፈሳዊ ሕይወት ያወራኝ ነበር፡፡ እኔም 13 አመት በሆነኝ ጊዜ አምኜ እንደዳንኩኝ እነግረው ነበር፤ እውነት አለመሆኑን ግን እኔም እርሱም እናውቅ ነበር፡፡

እኔ በትልቅ እምነትና መረዳት ውስጥ ነበርኩኝ፡፡ መዳን የሚለው ሐሳብ በአዕምሮዬ ውስጥ ቢኖርም እንኳ በተቻለኝ አቅም ለመቋቋም እታገል ነበር፡፡ በየካቲት ወር መጨረሻ አካባቢ ነገሩን መቋቋም አልቻልኩምና ጌታ እንዲያድነኝ ጠይኩኝ፡፡ እኔ የተረዳሁት ነገር ቢኖር በዚህ ጊዜ በዙሪያዬ ብዙ ሰዎች ስለ መዳኔ እንደሚጸልዩ ነው፡፡ የሚጸልዩልኝም ቤተሰቦቼ ብቻ ሳይሆኑ በቤተክርስቲያንም ያሉ አማኞች ጭምር ነበሩ፤ በሚገርም ሁኔታ ታናሽ ወንድሜ ጆሽ እንኳ ሳይቀር ወጣቶች ለእኔ እንዲጸልዩ አድርጎ ነበር፡፡ እግዚአብሔር የእነርሱን ጸሎት ስለመለሰ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ሪቼል ባረንቲኔ ለባለቤቱዋ ደህንነት እንድጸልይላት በምትጠይቀኝ ጊዜ ደስ በማይል ስሜት ውስጥ ነበረች። እርሱ ይጠጣ፣ ቁማር ይጫወትና ምሽቱን ሙሉ ውጭ ይቆይ ስለበር ጸሎቴ መልስ የለውም በሚል ስሜት ተሸነፈች። ሰይጣን እንደዚህ አይነት ስሜት እንዲሰማን የሚያደርገው እኛ ተስፋ ቆርጠን ጸሎት እንድናቆም ነው። እግዚአብሔር በአስደናቂ ሥራው አንዳንዴ አብሮነቱ እንኳ ሳይታውቅ ይህን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሰብሮ ይጥላል። ለጂምቦ ባረንታይን የሆነውም ነገር ይሄው ነው። እርሱ "ምንም እንኳ እኔ በዌስትውድ ባፕትስት ቤተክርስቲያን ባድግም እግዚአብሔር በእኔ ውስጥ የለም በሚል ስሜት ተሞልቼ ነበር።

ችግሮች እኔን ከእርሱ ይገፉ ነበር። ካገባሁና ወንድ ልጄን ከወለድኩ በኃላ እርሱን ወደ ቤተክርስቲያን ተመልሼ ያገኘሁ ቢሆንም፣ እያለፋሁ የነበርኩት በትልቅ ለውጥ ሂደት ላይ ነበር፤ ፍቺ ትክክለኛ እንደሆነ በውስጤ ትልቅ የራስ መተማመን ነበረኝና፣ ቤተሰብን ካጣሁ በኃላ የምድር ህይወቴ ሲኦል ሆነብኝ።

ራሔልን ካገባሁ በኃላ ኑሮ ጥሩ ይሆናል ብዬ ነበር፤ ነገር ግን ተሳስቻለሁ፤ በፍጹም ጥሩ አልነበረም። ነገሮችን የተወሳሰበ ለማድረግ እርሱዋ በጌታ አመነች። ከዚያም በውስጤ የነበሩ ክፉ ባህርያቶቼ ተባባሱ። እርሱዋ እኔን ለማሳመን የምትነግረኝ ነገር ላለመስማት ምሽቱን ሙሉ ስጠጣና ቁማር ስጫወት ውጭ አድር ነበር።

ማክሰኞ ዕለት፣ መጋቢት 13⁄2001 ምሽቱን ሙሉ ስጠጣና ስጨፍር፣ ቁማር ስጫወት ውጪ አድር ነበር። በማለዳ ረቡዕ ዕለት ወደ ቤት ስመጣ እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገኝ እንደዚህም መኖር እንዳለብኝ አውቄ ነበር። ወደ ቤተክርስቲያን ከወንድም ሊ ጋር ስለ መዳን ላወራ ሄድኩኝ፤ እርሱ ግን በከተማ ውስጥ አልነበረም። ስለዚህ ወደ አጎቴ ወደ ቦብ ቤት ሄድኩኝ። እርሱ በቤተክርስቲያን ሰባኪ እንደሆነ፣ እርሱና አውንት ፋዬ ሁለቱም ለእኔ ለረጅም ጊዜ እየጸለዩ እንደቆዩ ስለማውቅ በዚህ ጉዳይ እንደሚረዱኝ አውቅሁ።

አውንት ፋዬ (የእናቴ እህት) አንተ የእኔ ባል ሆነህ ቢሆን ኖሮ ከረጅም ጊዜ በፊት ተለያይተን ነበር ብላ መለሰችልኝ። ሚስቴ ራሔል በእኔ ተስፋ ስላልቆረጠች እጅግ አመሰግናታለሁ፤ በዚያ ረቡዕ ዕለት ጠዋት ነፍሴን

እንዲያድናት በክርስቶስ በፍጹም ታመንኩኝ፤ እርሱም ሕይወቴን በሚገርም ሁኔታ ቀየረልኝ።
እንባዎች "ፈሳሽ ጸሎቶች" ተብለው ይጠራሉ፤ ምናልባትም ከጸሎት ሁሉ የሚበልጡ ጸሎቶች ናቸው። እነርሱም ሐይለኛ እንዲሆኑ የተረዳሁት በሉሳና ሞሲ ብሉፍ ለብዙ ዘመናት በኦሪጌ ቴክሳስ የመገበኳትን አንዲት በጣም የምወዳት ሴት ቀብር ላይ አይቸዋለሁ። በዚህ ቀብር ላይ አንድ ሰው ወደ እኔ እየተራመደ መጣ፤ እጁን በመዘርጋት እየጨበጠኝ "እኔን አታውቀኝም አይደል?" አለኝ። እኔም "አይ ጌታዬ አይመስለኝ" አልኩኝ። እርሱም "እኔ የምኖረው በቡና ቴክሳስ ነው፤ በጋዜጣም ላይ ሊ ቶማስ ይሄንን የቀብር ሥነ-ሥርአት እንደሚያስፈጽም አየሁ። እኔም እኔ የማውቅህ ሊ ቶማስ እንደሆንኩኝ ለማረጋገጥ መጣሁ። እርሱም አንድ ታሪክ ነገረኝ "ስሜ ጀምስ ሊንች ይባላል። እኔ ያደግኩት በክርስቲያን ቤተሰብ ነው። በኦሪጌ ቴክሳስ በምኖርበት ጊዜ ግን የአልኮል ሱሰኛ ሆንኩኝ፤ ሥራዬንም ለመቀጠል በብዙ እታገል ነበር። አንድ ቀን በቤት ሳሎን ተቀምጬ ሳለሁ ብዙ ከመጠጣቴ የተነሳ በመሰቃየት ስለ ሕይወት ግራ ተጋብቼ ሳለሁ በሬ ተንኳኳ" አንተም ኢየሱስ እንደሚወደኝና ሊያድነኝ እንደሚፈልገኝ ነገርከኝ። ይሁን እንጂ እኔ በአልኮል ቁጥጥር ስር ስለሆንኩ፣ የእግዚአብሔርን ደህንነት ጥሪ አልቀበልም አልኩኝ።
አንተ ወንበሩ ሥር ተንበርክከህ አይኖችህ በእንባ ሞልተው ጭንቅላትህን ዝቅ አድርገህ ጌታ ኢየሱስ ስለሚያድንህ ተቀበለው ብለህ ለመንከኝ። ልቤም ተነካ እኔም ፈለኩኝ፣ ነገር ግን አልኮሉ ተቆጣጥሮኝ ስለነበር ማድረግ አልቻልኩም። ሶስት አመታት እነዚህ እንባዎች አሳደዱኝ። ንስሐ እንድገባና ጌታን እንድቀበል አንተ ያደረከውን በእግሮችህ ተንበርክከህ፤ እንባ አይኖችህን ሞልቶ ስትለምን ለአንዲት ቀን እንኳ በህልናዬ ሳላይ አልውልም ነበር። ለሶስት አመታት ከእግዚአብሔር ጋር ከታገልኩኝ በኃላ ንስሐ ገባሁ፣ እግዚአብሔርም በክብር አዳነኝ ለስብከትም አገልግሎት ጠራኝ። አሁን ለብዙ አመታት የእርሱን ቃል እየሰበኩ እገኛለሁ። አንተ በዚያ ቀን ወደ ቤት ባትመጣ ኖሮ ያለ እግዚአብሔር ጠፍቼና ሞቼ በሲኦል እሆን ነበር።
ለጆርጅ ሙለር ጓደኛውን ወደ ክርስቶስ በጸሎት ለመመለስ በየቀኑ የሚደረግ ጸሎት ከስልሳ አመታት በላይ ፈጅቷል። ጀምስ ሉንቺን ወደ ክርስቶስ

ለማምጣት ከሶስት አመታት በላይ የዘለቀ የእንባ ጸሎት ጠይቋል። ነገር ግን ሁለት ሺ የሚያህሉ ክርስቲያኖች በጸለዩለት ጊዜ ጃበዚ ኬሪ በመጀመሪያ ሰዓት ውስጥ ወደ ጌታ መጥቷል። ይህም የሚያሳየን በህብረት መጸለይ የጠፉት ወደ ጌታ እንዲመጡ ውጤታማ መንገድ እንደሆነ ነው።

ለማይክ ዶሌስ ደህንነት ይህ ቁልፍ ነገሩ ነበር። ታሪኩም ይህንን ይመስላል "እኔ ያደኩት በኒው ሆፐ ባፕትስት ቤተክርስቲያን ነው። ጌታ እኔን እንዲያድን በፍጹም አምኜ አላውቅም ነበር። በወጣትነት እድሜዬ ጓደኞቼ ጋር በመሆን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ጀመርኩ፣ ነገር ግን ውጤታማ አልነበርኩም። ወንድሞቼንና እህቴን በማየት ወደ ቤተክርስቲያን እሄድ የነበረ ቢሆንም፣ ውጤታማ አልነበርኩም። የዘላለም ሕይወት እንዳለ በዕውቀት ደረጃ አምናለሁ፤ ደግሞም በክርስቶስ ማመን ትክክለኛ ነገር እንደሆነ አማናለሁ፤ ሆኖም አላደርገውም ነበር።

ምንም እንኳ እናቴ ሳታቋርጥ ብትጸልይልኝም አንድ ቀን ምሽት የቤተክርስቲያን መጋቢው በጉባኤ ለአንድ ጌታን ለማያውቅ ሰው ጌታን እንዲቀበል ስሙን በወረቀት ላይ ጻፉ እስካለበት ጊዜ ድረስ ምንም ነገር አልሆነም ነበር። እርሱም በኃላ የነገረኝ ነገር ቢኖር ሰማንያ የሚያህሉ ወረቀቶችን እንደሰበሰበ፣ በእያንዳንዱም ወረቀት ላይ ስሜ መኖሩን ነው። እነርሱ ለእኔ መጸለይ ከጀመሩ ከጥቂት ጊዜ በኃላ በውስጤ ባዶነትና ከንቱነት ተሰማኝ፤ ይህም ስሜት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን አንክብካቤ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጌታን እስከመጠየቅ ድረስ እፎይታን አላገኘም።

እሁድ ማለዳ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ጀምሬ ነበር። አንድ ቀን መጋቢት 1/1998 እነዚህ አስራ ስምንት ልጆች ለእኔ መጸለይ ከጀመሩ ከሁለት ሳምንታት በኂላ፣ የመጀመሪያውን እርምጃ ብቻ ከተራመድኩ በኃላ ቀጥሎ ያሉትን እንደምረዳ ተናገረኝ፤ ይሄ ነገር ከጌታ ጋር ለነበረኝ ሕይወት ጅማሬው ነበር። ምንም እንኳ አርባ ዘጠኝ አመታትን ጌታን ለመቀበል ፍቃደኛ ሳልሆን በከንቱ ባሳልፍም፣ አሁን የተረዳሁት እንደ ክርስቲያን የእኛ ሥራ ቃሉን ለማሰራጨት የምንችለውን ነገር ሁሉ መጠቀምን ነው። እኔም እርሱ በሚሰጠኝ በማንኛውም ምቹ ዕድል በመጠቀም ይህንን ላደርግ ወስኛለሁ።

# ምዕራፍ 7

# ቃል ኪዳን ማድረግ

ይህ መጽሐፍ እንዲሁ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ ለመቀመጥ አልተዘጋጀም፤ በውስጡ ባሉ አስደናቂ እውነቶች ልብህን ዘልቆ ለመግባት እንጂ! የአንድ ሰው የዘላለም ሕይወት ጉዳይ በእጅህ ነው፡፡ አንተ የማትጸልይ ከሆነ ያ ሰው ሞቶ ወደ ሲዖል ይሄዳል፡፡ አንድሪው ሙሬ “መማለድ ምትክ የማይገኝለት፣ ነፍስን ለመለወጥ ዋናው ነገር ነው” ይላል፡፡ “አለም በብዙ ሚሊዮን ጠፊ ነገሮች ተሞልታለች፤ መማለድ ግን ብቸኛ ተስፋዋ ነው፡፡” ትንሽ ምልጃ ከመኖሩ የተነሳ ፍቅርና ሥራ ከንቱ ሆነዋል፡፡ ነፋሳት ከአለም ይልቅ ዋጋ ያወጣሉ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእነሱ ከተከፈለው ደም እኩል ዋጋ ያስፈልጋል፤ ይህም ደግሞ ሊገኝ የሚችለው በምልጃ ጸሎት ውስጥ ነው” (ሙሬ፣ 112)፡፡

እኔ ለአንተ የምጸልየው ይህን መጽሐፍ ስታነብ በውስጡ ባለው እውነት ርህራሄ ተፈጥሮ እግዚአብሔር እንደሚፈልግህ ለጠፉት የምትማልድ አይነት ሰው እንዲያደርግህ ነው፡፡ በሳንድራ ጉድ ዊን የተጻፈውን የሚቀጥለውን ግጥም ስታነብ፣ በልብህ ጌታ ሆይ እኔ ሥራውን እሰራለሁ እንደሚል ተስፋ አደርጋለሁ!

**በጉልበቶቼ መራመድ**

ትናንት ማታ ተጉዤ ነበር
ከባህር ማዶ ወዳለች አገር
በመርከብ በአውሮፕላን አደል የሄድኩት
በጉልበቶቼ እንጂ የተጓዝኩት፡፡
በዚያም አየሁ ብዙ ሰዎችን
በኃጢአታቸው ምክንያት የታሰሩትን፣
ኢየሱስም ነገረኝ እንዲሄድ ወደ እነርሱ
የሚድኑ ነፍሳት ስላሉት እርሱ፡፡
ግና "ኢየሱስ መሄድ አልችልም" አልኩ ለእኔ ከብዶ
ባሕር ተሻግሬ መሄድ ማዶ፣ እርሱ ግን መለሰለኝ "አዎን ትችላለህ"
በጉልበቶችህ ተራምደህ፡፡
በጉልበቴ ተንበርክኬ ሳለ
አቅሜ እጅጉን ዛለ
ጌታ ግን በአጠገቤ ቆሞ አየሁት
በጉልበቴ ተራመድኩ በጸሎት፡፡
ስጸልይ አየሁ ሲድን ነፍስ
የታመመ ሰው ሲፈወስ፡፡
አየሁ አገልጋዮቹ ሲበረቱ
በመስክ ስራ ላይ ያሉቱ፡፡
አልኩኝ እኔም "ጌታዬ ሆይ ሥራውን እሰራለሁ"
ያንተንም ልብ አስደስታለሁ፡፡
ድምጽህን ሰምቼ ወዲያው እሄዳለሁ፤
በጉልቤቶቼ እንበረከካለሁ፡፡"
(ሉንድስትሮም 207-208)

እግዚአብሔር ለእኔ የሰጠኝ ሸክም በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ እየበዙ የሚሄዱ የእግዚአብሔር ሰዎች ለነፍሳት በምልጃ ጸሎት ተዋጊ የጸሎት ሰራዊቶች እንዲሆኑ ነው፡፡ አንባቢ ሆይ! በብዙ የምባርክዎ ለጠፉ ነፍሳት በሚደረግ

የክብር፣ የኃይልና ውጤታማ ጸሎት መቀላቀልዎን እኔ እንዳውቅ ሲያደርጉ ነው።
ስለሆነም ትኩረት አድርገው እንዲድን የሚፈልጉት ሰው ካለ ስሙንና ከእርስዎ ጋር ያለውን ዝምድና፣ ይህ ሰው ስላለበት ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ ከላኩልኝ ጌታ በማቴዎስ 18፡19 ላይ በሰጠው የተስፋ ቃል መስረት እኔም ከእርስዎ ጋር በመስማማት እጸልያለሁ። ይህን የማደርገው ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጠቀስኳቸው የጸሎት መርሆዎች መሰረት የሚጸልዩ ከሆነ ነው። እግዚአብሔር በዚህ ሰው ዙሪያ በተለይ ወደ ደህንነቱ እየተቃረበ መሆኑንና እየሰራ የሚያሳይ መረጃ መስጠት አለብዎ!

# የጸሎት ርዕስ ቅጽ

***1ኛ ሳሙኤል 12፡23 ፦***

“ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ”

1. ______________________________
______________________________
2. ______________________________
______________________________
3. ______________________________
______________________________
4. ______________________________
______________________________
5. ______________________________
______________________________
6. ______________________________
______________________________
7. ______________________________
______________________________
8. ______________________________
______________________________
9. ______________________________
______________________________
10. ______________________________
______________________________
11. ______________________________
______________________________

12. ______________________________________________

______________________________________________

13. ______________________________________________

______________________________________________

14. ______________________________________________

______________________________________________

15. ______________________________________________

______________________________________________

16. ______________________________________________

______________________________________________

17. ______________________________________________

______________________________________________

18. ______________________________________________

______________________________________________

19. ______________________________________________

______________________________________________

20. ______________________________________________

______________________________________________

21. ______________________________________________

______________________________________________

22. ______________________________________________

______________________________________________

23. ______________________________________________

______________________________________________

24. ______________________________________________

______________________________________________

# ዋቢ መጻሕፍት

Billheimer, Paul E. Destined to Overcome. Minneapolis: Bethany House, 1982.

Blanchard, Charles. Getting Things from God. Chicago: Moody, 1934.

Carre, E. GPraying Hyde. South Plainfield: Bridge, n.d.

Chadwick, Samuel. The Way To Pentecost. Fort Washington: CLC, 2001.

Charter Lewis S. True Evangelism. Findley: Durham, 1919.

Chambers Oswald.If Ye Shall Ask. Alexandria: Lamplighter, n.d.

Christenson Evelyn. Battling the Price of Darkness. Wheaton: Victor, 1990.

Cymbala, Jim. Fresh Wind, Fresh Fire. Grand Rapids: Zondervan, 1997.

Deuwel, Wesley. Mighty Prevailing Prayer. Grand Rapids: Asbury, 1990.

Dunn, Ronald. Don't Just Stand There, Pray Something.Nashville: Nelson, 1992.

Eastman, Dick. No Easy Road.Grand Rapids: Baker, 1971.

Edwards, Brain. Rivival.Durham: Evangelical, 1990.

EPP, Theodore H. Praying with Authority: Lincoln: Bible Broadcast, 1965.

Finney, Charles G. Revivals of Religion. Old Tappan: Revell, n.d. Charles

G. Finney: An Autobiography. Westwood: Revell, 1876

Gordon, A. J. The Holy Spirit in Missions. New York: Revell, 1903.

Gordon, S.D. Quiet Talks on Prayer. New York: Revell, 1903.

Huegel, FJ. Prayer's Deeper Secrets. Grand Rapids: Zondervan, 1959

Lundstrom, Lowell. How You can Pray with Power and Get Results.Sisseton: Lundstrom Ministries, 1981.
Matthews, R. Arthur. Born For Battle. Wheaton: Shaw, 1978.
McClure, James G.K. Intercessory Prayer. Chicago: Moody, 1978.
Murray, Andrew. The Ministry of Intercession.Old Tappan Revell.n.d
Newell, Philip.Revival on God's Terms. Chicago: Moody, 1959.
Penn —Lewis, Jessie.Prayer and Evangelism. Dorset: Overcomer, n.d.
Pierson, A.T. George Muller of Bristol. Old Tappan: Revell, 1989.
Ravenhill, Leonard. Revival God's Way. Minneapolis: Bethany House, 1986.
Smith, Eddie. Intercessors: Houston: Spirit Truth, 1998.
Spurgeon, Charles. My Conversation. Springdale: Whitaker, 1996.
Twelve Sermons on Prayer, Grand Rapids: Baker, 1990
Steer, Roger. George Muller: Delighted in God. Wheaton: Shaw, 1986.

*ማስታወሻ ፡-*

*በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር አንባቢው በቀጥታ እንዲያገኛቸው በማሰብ በእንግሊዘኛው እንዳለ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡*

ለጠፉት ሰዎች መጸለይ በብዛት ተደጋግሞ የተነገረ ሐሳብ ነው፤ ይሁን እንጂ እውቀቱና መረዳቱ ጥቂት ነው። ይህ በሚስጥራዊ ቁጥር የተዘጋ ካዝና ቁጥሩን ሳያሳውቁ ለመክፈት እንደመሞከር ይቆጠራል፤ ምንም ያህል ሙከራ ብናደርግ ተስፋ እንቆርጣለን ፣ እናቆማለንም ። ለዘላለም መንግስት ለማዘጋጀት ክርስቶስ የሞተላቸው ነፍሳት ቁም ነገሮቻችን ሊሆኑ ይገባል፤ ለእነርሱ ውጤታማ ጸሎት እንዴት ማድረግ እንዳለብን መማር ይኖርብናል

(ከመጽሐፉ የተወሰደ)

ለጠፉት ነፍሳት ያለን ፍቅር እንድንጸልይላቸው ከሚያደርጉ ውድ ምክንያቶች የመጀመሪያው ነው። ጸሎት "ፍቅር በጉልበቷ ላይ" እንደሆነች ማሳያ ፣ በአለም ላይ ካሉ ነገሮች ኹሉ ይልቅ ተጽዕኖ አድራጊ ኃይል ያለው ትዕዛዛዊ ሥራ ነው። ክርስቲያን ሲጸልይ መልካምን ሁሉ ለመሥራት ብሎም ወደ ውጤታማነት ለመድረስ ያለው ችሎታ ሺህና መቶ ሺህ እጥፍ ይጨምራል፤ ይህ ማጋነን አይደለም! ሰው ሲጸልይ እግዚአብሔር ይሰራል።

(ከመጽሐፉ የተወሰደ)

ኢየሱስ ክርስቶስ ለጠፉት ነፍሳት የውጤታማ ጸሎት ዋና ምሳሌያችን ነውና.... አንባቢያን ይህን ግሩም መጽሐፍ ገንዘባቸው በማድረግ ለብዙዎች መዳን ተዋጊ የጸሎት ስራዊቶች እንዲኾኑ፣ በዚህም ለጠፉ ነፍሳት በሚደረግ የክብር እና የኃይል ውጤታማ ጸሎት እንዲቀላቀሉ በእጅጉ እናበረታታለን።

(አናሲሞስ አገልግሎት)

ዋጋ 50 ብር

Design & Print Glory Printing Service
+2519 44182525 | +251 912461654